የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን

# የ2014 በጀት ዓመት

# ዓመታዊ የድርጊት መርሃ-ግብር/ዕቅድ

---

**ሐምሌ 2013 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

## ማውጫ


**መግቢያ ........ 3**

**የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም አጭር ግምገማ ........ 4**

**1. የለውጥ እና ተቋም አቅም ግንባታ እርምጃዎች አፈጻጸም ........ 4**

1.1 የተቋም አቅም ግምገማና የአቅም ግንባታ ዕቅድ ........ 4

1.2 አዲስ መዋቅር ጥናት ........ 6

**2. የመደበኛ ተግባራት የ2013 በጀት ዓመት ዋናዋና ክንውኖች ........ 8**

2.1 የሰብአዊ መብቶች ትምህርር እና ስልጠና ማሳደግ ........ 8

2.2 የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ክትትል እና ምርመራ ........ 12

2.3 ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ........ 24

2.4 የ2013 በጀት አመት የፋይናንስ አጠቃቀም ........ 35

**3. የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ጥቅል ግምገማ ........ 35**

3.1 ጥንካሬዎች ........ 35

3.2 ተግዳራቶች ........ 36

**4. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ........ 38**

4.1 የኮሚሽኑ ራዕይ፣ ተልእኮ እና እሴቶች ........ 38

**5. የዕቅዱ ዓላማ ........ 39**

**6. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ስትራቴጂያዊ ማዕቀፍ ........ 39**

**7. ቁልፍ የውጤት መስኮች ........ 39**

**8. የፕሮግራም መስኮች ........ 41**

**9. የ2014 ዕቅድ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ........ 46**

**10. በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች እና መፍትሄዎች ........ 46**

**11. የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ........ 47**

11.1 የዕቅድ አፈጻጸሙ የክትትል ስርዓት ........ 47

11.2 ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ በጀት ........ 48

11.3 የዕቅድ ማስተግበሪያ መርሃ-ግብር ........ 49

የፕሮግራም መስክ 1: የሰብአዊ መብቶች ትምህርት ........ 50

የፕሮግራም መስክ 2፡ የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ ........ 55

የፕሮግራም መስክ 3 ፡ የሴቶች እና ህጻናት መብቶች አፈፃፀም ይጠናከራል እንዲሁም የመብቶች ጥሰቶች አጥጋቢ መፍትሔ ያገኛሉ፤ ....... 58
ፕሮግራም መስክ 4፡ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች አፈፃፀም ይጠናከራል፤ የመብቶች ጥሰትም ውጤታማ መፍትሄ ያገኛል፤ ....... 65
የፕሮግራም መስክ 5፡ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች አተገባበር ይጠናከራል፤ የመብቶች ጥሰቶችም ተገቢውን መፍትሄ ያገኛሉ ....... 74
የፕሮግራም መስክ 6: የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች አተገባበር የዕጠናከራል፤ የመብት ጥሰቶች ተገቢውን መፍትሄ ያገኛሉ፤ ....... 80
ፕሮግራም መስክ 7፡ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች (ኢማባመ) አተገባበር ይጠናከራል፤ የመብት ጥሰቶች ተገቢውን መፍትሄ ያገኛሉ ....... 84
ፕሮግራም መስክ 8፡ ኮሙኒኬሽን ኢኮቴ እና አጋርነት (Communications, ICT and partnership) ....... 90
የፕሮግራም መስክ 9፡ ተቋማዊ ሪፎርም አቅም ግንባታና ቀጣይነት ....... 97

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በፌደራል ሕገ መንግስቱ አንቀፅ 55(14) መሰረት ነጻ ፌደራላዊ መንግስት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመናለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የሚሰራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው።በ2012 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁጥር 1224/2012 የኢሰመኮን ተቋማዊ አደረጃጀት እና ነፃነት ለማጠናከር የሚረዱ ማሻሻያዎች በማቋቋሚያ አዋጁ (አዋጅ ቁጥር 210/2000) ላይ ተደርገዋል።

በዚሁ መሰረት በ2012 እና 2013 ዓ.ም. ሲካሄድ የነበረው የኢሰመኮ የለውጥና የተቋም አቅም ግንባታ በተሟላ ፕሮግራም እየታገዘ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። ኮሚሽኑ በተሰጠው ስልጣን እና ኃላፊነት መሰረት የሚያከናውናቸውን ተግባራት እንዲመራ በማሰብ አሁን ካሉት እና ወደፊት ሊከሰቱ ይችላሉ ከሚባሉ ብሔራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም-አቀፋዊ ሁኔታዎች አንጻር የተቃኘ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ /2014-2018/ በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱ ዝግጁቱን አጠናቋል። አዲሱ ስትራቴጂክ ዕቅድ በሀገሪቱ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ታሳቢ ያደረገ እና በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንዲጠናከር ከተደረገው የኮሚሽኑ ስልጣንና ኃላፊነት ጋር የተጣጣመ ነው።

ኮሚሽኑ በዚህ ስትራተጂክ እቅድ ላይ ተመስርቶ የ2014 በጀት አመት እቅድ አዘጋጅቷል። ይህ የ2014 በጀት አመት እቅድ ኮሚሽኑን በሕግ የተሰጠውን ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የመስራት ተልዕኮዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትና ውጤቶችን የያዘ ነው። በተጨማሪም ነባሩን መዋቅራዊ አደረጃጀት ፈትሾ በማስተካከል አዲሱ መዋቅር በሚጠይቀው የብቃትና የልምድ ደረጃ የሚመጥኑ ፈጻሚ ሙያተኞችን በማሟላት የማሰራት፤ የተቋሙን ቀጣይ አምስት ዓመታት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በተመለከተ በሁሉም የተቋሙ አመራሮችና ፈጻሚዎች ግንዛቤ በመፍጠርወደ ተግባር ስራ መሸጋገር እንዲሁም የአመራሩንና ፈጻሚውን ሙያና ክህሎት አቅም ማጠናከር ትኩረት ሰጥቶ ሊፈፅማቸው ያቀዳቸው ተግባራት ናቸው።

# የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም አጭር ግምገማ

## 1. የለውጥ እና ተቋም አቅም ግንባታ እርምጃዎች አፈጻጸም

### 1.1 የተቋም አቅም ግምገማና የአቅም ግንባታ ዕቅድ

በኮሚሽኑ ለሚደረገው የለውጥ እና የተቋም አቅም ግንባታ ስራዎች መነሻ ሊሆን የሚገባው ተቋሙ በእስካሁን ጉዞው የነበረው ጠንካራ ጎን እና ድክመት፣ በአሁኑ ወቅት ያለው አቅም እና የአቅም ውስንነት እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ተግዳሮቶችን ለይቶ ማወቅ ነበር።

በዚህ መሰረት የኮሚሽኑን ተቋማዊ አቅም (institutional capacity) በሚመለከት በተገቢው መንገድ ግምገማ እንዲከናወን ለማድረግ በጉዳዩ ላይ በቂ ልምድና እውቀት ያላቸውን ድርጅቶችና ባለሙያዎች በማሰባሰብና፤ ኮሚሽኑን ከተጨማሪ ወጪ ለመጠበቅም ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጪ እና የባለሙያ ድጋፍ ከለጋሽ ድርጅቶች በማፈላለግ የተቋም አቅም ግምገማው በተሳካ መንገድ ተከናውኗል።

በተለይም በዓለም አቀፍ እና በአፍሪካ አህጉር ደረጃ ተመሳሳይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎችና ተቋማት ጋር በመተባበር ለአቅም ግንባታ እቅዱ አስፈላጊ መረጃዎችና ግብዓቶች ተሰብስቧል።

በዚህ ጥናት መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት17 አጠቃላይ የተቋም አቅም ግንባታ ዘርፎች የተለዩ ሲሆን፤ በእነዚህ ወሳኝ ዘርፎች ላይ የተነደፉ የአቅም እና አዲስ የአሰራር ስልት ግንባታ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ የ2014 በጀት ዓመት ቁልፍ ስራ ነው።

- ምቹ የሕግ ማዕቀፍ (Enabling legislation) ፦ ከዚህ በታች እንደተገለጸው ለኮሚሽኑ የለውጥ ትግበራ አስፈላጊ የነበረው የሕግ ማዕቀፍ በ2012 ዓ.ም. ማብቂያ ላይ የጸደቀ በመሆኑ ዋነኛው ስራ የተከናወነ ቢሆንም፤ ስለአዲሱ የሕግ ማዕቀፍ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠርና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ ቀጣይ ስራዎች ናቸው፣

- የአመራር አቅም ግንባታ (Leadership)
- የበጀት አቅም ግንባታና ተያያዥ ጉዳዮች (Budget and Related Issues)
- የመዋቅር ለውጥ (Restructuring)
- የሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ ማስፋፋት (Human rights promotion activities)
- የእስር ቤቶች ክትትል (prisons and detention facilities monitoring)
- አቤቱታን ማስተናገድና የምርመራ ሥራ (Complaint handling and investigations)
- ምክረ ሃሣብ ማቅረብና አፈፃፀማቸውን መከታተል (Issuing recommendations and follow up)
- አፋጣኝ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ላይ ክትትል ማድረግ (Responsiveness to urgent human rights issues)
- የመንግስት አካላትን ማማከር (Advising state institutions)
- ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በትብብር መስራት (Cooperation with civil society)
- ከዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና ስልቶች ጋር መስራት (Engagement with international and regional human rights mechanisms)
- ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች እንዲፀድቁና በብሔራዊ ደረጃ እንዲፈፀሙ መጎትጎት (promoting ratification of all international human rights instruments and their national implementation)
- የስትራቴጂ እቅድና ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች (strategic plan and priorities)
- የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል አዎንታዊ ተፅዕኖ ማድረግ (Impact on the human rights situation)
- የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በእውቀት፣ ክህሎት እና ስነ-ዘዴዎች አጠቃቀም ማብቃት (Staff competences in knowledge, skills and methods)
- የመረጃ፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና ኮሙኒኬሽና ሚድያ (ICT, communication and media)

## 1.2 አዲስ መዋቅር ጥናት

የመዋቅር ስራን ማጠናቀቅና ትግበራ መጀመር በ2013 ዓ.ም. ኮሚሽኑ ሊያከናውናቸው ካቀዳቸው የተቋም ግንባታ ስራዎች አንዱና ዋነኛው በመሆኑ የመዋቅር ጥናት የሚያጠና አማካሪ ድርጅት ተቀጥሮ የጥናት ስራው ተጠናቋል። የመዋቅር ጥናቱ በአጠቃላይ 7 ወር የፈጀ ሲሆን ጥናቱ በኮሚሽኑ እንዲመጣ የሚፈለገውን የተቋም ግንባታ በተጨባጭ እንዲያግዝ በማሰብ በጥንቃቄና በጥራት ተከናውኗል። በአመራር ቦታ ላይ ያሉ ሁሉም ሰራተኞችና ሌሎች ጥናቱን ሊያግዙ፤ ግብዓትና አስተያየት ሊሰጡ የሚችሉ ሰራተኞች እየተለዩ በጥናቱ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል።

የመዋቅር ጥናቱ ዋና ዋና ቁልፍ ተግባራት መጠናቀቅን ተከትሎ፤ የተከናወኑ ተግባራትና ቀጣይ እርምጃዎችን በተመለከተ የጽሁፍ መልዕክት/ማብራሪያ ለሁሉም የኮሚሽኑ ሰራተኞች (የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችን ጨምሮ) በኢሜልና በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ በመለጠፍ ወቅታዊ መረጃ ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል።

ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላትና ከኮሚሽኑ ሰራተኞች በተገኘ አስተያየት መሰረት የኮሚሽኑ ሰራተኞች (የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችን ጨምሮ) እየተከናወነ ያለውን የመዋቅር ስራ ያለበትን ደረጃ፣ የተከናወኑ ተግባራትና ቀሪ ስራዎችን በተመለከተ የተለያዩና ተከታታይነት ያላቸው የምክክር መድረኮች ተካሂደዋል። በውይይቱም ሰራተኞች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ በሚመለከታቸው አካላት ተስጥቷል፤ በአንዳንድ መድረኮች የተነሱ ምክንያታዊና ጠቃሚ አስተያየቶችም የመዋቅር ጥናቱ እንዲካተቱ ሆነዋል። በተደረጉት የምክክር መድረኮች የኮሚሽኑን የወደፊት ከፍተኛ መዋቅር፤ የተለያዩ የሥራ ከፍሎችና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መዋቅር ምን እንደሚመስልና አሁን ካለው መዋቅር ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት ለሰራተኞች ገለፃ ተደርጓል። በቀጣይም የአዲሱ መዋቅር ትግበራን በሚመለከትና ከትገበራው ጋር በተያያዘ ከሰራተኞች ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያና ገለፃ የሚካሄድ ይሆናል።

በተጨማሪም በመዋቅሩ ውስጥ ለተካተቱት ለሁሉም የሥራ መደቦች የሥራ መዘርዝር ዝግጅት፤ የሥራ መዝርዝሮችን መሰረት ያደረገ የሥራ ምዘና/ከፍታ ግምገማ፣ የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም

የገበያ ጥናትና መዋቅሩን በ2014 የበጀት ዓመት ለመተግበር የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያና የሃብት ማሰባሰብ ሥራ ተከናውኖል።

የመዋቅር ስራው በሶስት ወራት እንዲጠናቀቅ የታሰበ ቢሆንም ሰባት ወራትን ፈጅቷል። በተያዘለት የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቁ የኮሚሽኑን አፈፃፀም ከእቅድ በታች ያደረገው ሲሆን በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቅ ያጋጠሙት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ፕሮጀክቱን ለመፈፀም የተያዘው የጊዜ ገደብ ከስራው ስፋት አንጻር አጭር በመሆኑ ተጨማሪ ጊዜ ሰጥቶ መስራቱ የጥናቱን ጥራት እንደሚጨምረው በመታመኑ፤
- የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ መዘግየቱና መዋቅሩ በማሻሻያ አዋጁ የሚመጡትን ለውጦች ማካተት ስላለበት፤
- የኮሚሽኑ የአምስት አመት መሪ ዕቅድ መጠናቀቁና የተቋም መዋቅር በተፈጥሮው መሪ ዕቅድ ላይ መሰረት ማድረግ ስላለበት ያንን ክፍተት ለመሙላት ሌሎች ተጨማሪ የምክክር መድረኮች በማስፈለጋቸው፤
- አማካሪ ድርጅቱ የሚያቀርባቸውን ስራዎች መርምሮ ግብአት እንዲሰጡ የሚጠበቁ ሰራተኞች በሌሎች ስራዎች መያዛቸውና በአጠቃላይ የአቅም ውስንነት በመኖሩና ጥናቱን በተቻለ መጠን አሳታፊ ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ጨምሮ ሌሎች በየደረጃው ሲያጋጥሙ የነበሩት ችግሮች ከአማካሪ ድርጅቱና ከኮሚሽኑ አመራሮች ጋር በመወያየት በየደረጃው የመፍትሄ እርምጃዎች ተወስደዋል።
የመዋቅር ጥናት ማጠናቀቅና ትግበራ መጀመር ኮሚሽኑ በ2013 ሊያከናውናቸው ካቀዳቸው የተቋም ግንባታ ስራዎች አንዱና ዋንኛው በመሆኑ የታቀደውን የኮሚሽኑን የተቋም ግንባታ ዕቅድ አሳክቷል።

# 2. የመደበኛ ተግባራት የ2013 በጀት ዓመት ዋናዋና ክንውኖች

## 2.1 የሰብአዊ መብቶች ትምህር እና ስልጠና ማሳደግ

ከዋናው መ/ቤት እና ከቅ/ጽ/ቤቶች ለተወጣጡ 30 ወንዶች እና 5 ሴቶች በድምሩ 35 የሰብአዊ መብቶች ስልጠና እና ግንዛቤ ባለሙያዎች በሴቶችና ህጻናት መብቶች የማሰልጠኛ ማኑዋልና የአሰልጣኝ መምሪያ ላይ ለ5 ቀናት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። ባለሙያዎቹ በወሰዱት ስልጠና መሰረትም አንድ ዙር በማሰልጠን ለሁለተኛ ዙር ስልጠና በዝግጅት ላይ ናቸው። በዚህም መሰረት፡-

በዋናው መ/ቤት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በስሩ ካሉ ከ11ዱም ክፍለ ከተሞች ለተወጣጡ 10 ወንዶች እና 25 ሴቶች በድምሩ 35 የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ፅ/ቤቶች አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና ከሀረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከሴቶችና ህጻናት፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ፣ ከጤና፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ እና ከትራንስፖርት ቢሮዎች፣ ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ከማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እና ከፖሊስ ኮሚሽን ከእያንዳንዱ ተቋም 2 አመራርና ባለሙያ ተጋብዞ በድምሩ ለ25 (ወንድ 9 እና ሴት 16) ሰልጣኞች በሴቶችና ህጻናት መብቶች ላይ አዲስ በተዘጋጀው የማሰልጠኛ ማኑዋል እና መመሪያ መሰረት ስልጠና ተሰጥቷል። ሰልጣኞች በተቋም ደረጃ ውይይት በማድረግ ዕቅድ ውስጥ በማካተትና በበጀት አስደግፎ ስልጠናውን ለመስጠት በዝግጅት ላይ ናቸው።

በኢሰመኮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት በሴቶችና ህጻናት መብቶች ዙሪያ ከሴቶች ማህበራትና አደረጃጀቶች፣ ከሴቶችና ህጻናት ጽ/ቤቶች፣ ከፍትህ አካላት፣ ከሕግ አስከባሪ አካላት እና ከተለያዩ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት ለተውጣጡ ወንዶች 210 ሴቶች 179 በድምሩ 389 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

ከዳኒሽ የሰብአዊ መብት ተቋም (Danish Institute for Human Rights) ጋር በመተባበርና የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከሰላም፣ አብሮነትና መቻቻል አንጻር ለወጣቶች የሰብአዊ መብቶች

ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል ማኑዋል ተዘጋጅቶ ከዋናው መ/ቤት እና ከቅ/ጽ/ቤቶች ለተውጣጡ 26 ወንዶች እና 3 ሴቶች በድምሩ ለ29 የኮሚሽኑ ሰብአዊ መብቶች ትምህርት ባለሙያዎች ለ5 ቀናት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል። ሰልጣኞችም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ የመጀመሪያ ዙር ስልጠና ለመስጠት ቅደመ-ዝግጅት ላይ ይገኛሉ።

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት ከፍትህና ሕግ አስከባሪ ተቋማት ለተውጣጡ 49 ወንዶች እና 16 ሴቶች በድምሩ ለ65 አመራሮችና አባላት በተጠርጣሪዎች እና ታራሚዎች መብቶችና አያያዝ ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል። በተመሣሣይ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት የተጠርጣሪዎችና ታራሚዎችን መብቶችና ግዴታዎች አስመልክቶ ለ1316 ወንዶች እና ለ189 ሴቶች በድምሩ 1505 ተጠርጣሪዎችና ታራሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ለተውጣጡ 50 ወንዶች እና 30 ሴቶች በድምሩ 80 ሰልጣኞች በመሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች ፅንሰ-ሀሳብ ላይ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም የሰብአዊ መብቶችና ግጭት አፈታትን አስመልክቶ ለ25 ወንዶች እና 13 ሴቶች በድምሩ ለ38 የሴቶች እና ወጣቶች ማህበራትና ፌደሬሽኖች አባላት ስልጠና ተሰጥቷል።

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት በ4 ርዕሰ ጉዳዮች (የተጠርጣሪዎችና የታራሚዎች መብቶችና አያያዝ፣ የሰብአዊ መብቶችና ግጭት አፈታት እና መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት) ላይ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ተከናውኗል።

ከባለድርሻ አካላት በቀረበ ጥያቄ መሰረት ለ22 ወንዶች እና ለ3 ሴቶ በድምሩ ለ25 የዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሰራተኞች እና የስራ ሀላፊዎች በ Business and Human Rights ርዕስ ላይ የሁለት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል። በተመሳሳይ መንገድ ለ30 ወንዶች እና 4 ሴቶች በድምሩ ለ34 የፌዴራል መንገዶች ባለስልጣን አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና የግል ዘርፉ ባለድርሻ አካላት በሰብአዊ መብቶች ጽንሰ-ሃሰብና ከትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ አንጻር ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ

የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶች ዙሪያ ከተሰጣቸው ኃላፊትና ተግባር ጋር በማስተሳሰር የሁለት ቀናት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

## በምርጫና ሰብአዊ መብቶች ላይ ግንዛቤ መፍጠር

በኢሰመኮ ምርጫና ሰብአዊ መብቶች ስቲሪንግ ኮሚቴ አስተባባሪነት ለ30 ባለሙያዎች በምርጫ ሂደት የፀጥታ አካላት ሚና በሚል ርዕስ የሁለት ቀን የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል። ሰልጣኞች ለማሰልጠን የሚያስችል ቅድመ-ዝግጅት አጠናቀው ስልጠና መስጠት ጀምረዋል።

ከምርጫ ክትትል ስቲሪንግ ኮሚቴ ጋር በመተባበር በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ከሚሳተፉ ከ50 በላይ የተፎካካሪ ፓርቲዎች አመራሮች ጋር በምርጫ ወቅት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ባለ6 ነጥብ የሰብአዊ መብት አጀንዳዎች ላይ ውይይት ተደርጓል። በዚህም መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የሰብአዊ መብት አጀንዳዎቹን በማኑፌስቷቸው በተገቢው ሁኔታ በማካተት ለመተግበር ቃል ገብተዋል። ባለ6 ነጥብ የሰብአዊ መብት አጀንዳዎቹን እና የፖለቲካ ፓርቲዎቹን ቃልኪዳን ለህብረተሰቡ ይበልጥ ለማስተዋወቅ ይረዳ ዘንድ ከፋና ብሮድካሰቲንግ ኮረፖሬት ጋር በመተባበር ሁለት የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው እንዲተላለፉ ተደርጓል።

## የሰብአዊ መብቶች ክበባት ክትትል እና ድጋፍ

የሰብአዊ መብቶች ክበባትን በትምህርት ቤቶች ለማደራጀትና ለማጠናከር በተከናወነ ሥራ በ50 የ1ኛ ደረጃ እና በ5 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰብአዊ መብቶች ክበባትን የማደራጀትና የገለፃ ሥራ ተከናውኗል።

## የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የምስለ-ፍርድ ቤት ውድድር

ከትግራይ እና ከጋምቤላ ክልሎች በስተቀር በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የተሳተፉበት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የምስለ-ፍርድ ቤት ወድድር በክልል ደረጃ ተካሄዶ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ ከ8 ክልሎች እና ከ2 ከተማ አስተዳደር አሸናፊ የሆኑ ተማሪዎች ለኮሚሽኑ የላኩት የመከራከሪያ ፅሁፍ (Essay) በኮሚሽኑ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ባለሙያዎች አማካኝነት ታርሞ ባገኙት ውጤት መሰረት የቤኒሻንጉል፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔሮች፣

ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ የሲዳማ፣ የሀረሪ እና የሶማሌ ክልሎች እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ተወዳዳሪ ተማሪዎች በማለፋቸው በሀገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው ወድድር እንዲሳተፉ ተደርጓል። ውድድሩም የተወዳዳሪ ተማሪዎች አማካሪ መምህራን፣ ወላጆች፣ የት/ቢሮ ተወካዮች፣ የኢሰመኮ ዋናው መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤት የተወከሉ ባለሙያዎች እንዲሁም በመጨረሻው ቀን ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት በ3 ዙር ውድድር የዳኝነት ልምድ ባላቸው ከፍተኛ ባለሙያዎች ተካሂዶ አዲስ አበባን በመወከል ከመነን የሴቶች አዳሪ ት/ቤት የመጡ ተማሪዎች አሸናፊ ሆነዋል። የመጨረሻው ውድድር የኮሚሽኑን መልዕክት ባካተተ መልኩ የሚዲያ ሽፋን አግኝቶ ህብረተሰቡ ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲያገኝበት ለማድረግ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር በመተባበር የቴሌቪዥን ፕሮግራም ተሰርቶበታል። ከተደረገው የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር ጠንክራና ደካማ ጎን በመለየት ለቀጣይ ጊዜያት ለማሻሻል ትምህርት ተወስዶበታል።

### በመደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን ለማካተት የቅድመ-ዝግጅት ሥራ

ከዳኒሽ ሰብአዊ መብቶች ተቋም (Danish Institute for Human Rights) ጋር በመተባበር የሰብአዊ መብቶች ትምህርት በኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ እና ካሪኩለም መካተቱን ለመገንዘብ የሚያስችል መረጃ በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ከ10 የአፍሪካ ሀገራት የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጋር ውይይት በማድረግ በሶስት ዙር በዌብነር በተሰጠ ስልጠና የኢሰመኮ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል። በተመሳሳይ መልኩ ከዚሁ ተቋም ጋር በመተባበር የሰብአዊ መብቶች ማሰልጠኛ ማኑዋል አዘገጃጀትን በተመለከተ አማካሪዎችን ባሳተፈ መልኩ በ2 ዙር በዌብነር ስልጠና ላይ መሳተፍ ተችሏል።

በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰብአዊ መብቶች ትምህርት አሰጣጥን በተመለከተ ጥናት በማካሄድ በጥናቱ ውጤት ሌይ ከፌዴራል እስከ ክልል የሚገኙ የሰርዓት-ትምህርት ባለሙያዎችንና ሌሎች በፌዴራል የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ወርክሾፕ በማዘጋጀት ውይይት ተደርጓል። በዚህም ሰነዱን የማዳበር ስራ ከመሰራቱም ባሻገር የውትወታ ስራ በማከናወን የሰብአዊ መብቶች ትምህርት በመደበኛ ትምህርት እንዲካተት የኮሚሽናችን ዋና ኮሚሽነር እና የትምህርት ሚኒስቴር ሚንስትር በጋራ በመምከር በጋራ ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችል የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል።

**ኮቪድ 19 እና ሰብአዊ መብቶች**

ሰብአዊ መብቶች እና ኮቪድ 19ን አስመልክቶ በ8 ርዕሶች ላይ የተዘጋጁ ጽሁፎችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በተደረገው ጥረት በቃለ-መጠይቅና በአጭር መልዕክት (spot) መልክ የተዘጋጀውን ፕሮግራም በትምህርት ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቴሌቪዢን ስርጭት ላይ እንዲተላለፍ ተደርጓል። በዚህም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ተሞክሯል።

ኮሚሽኑ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ እና ከታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር ተያይዞ የሰራቸውን የክትትል እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ያወጣቸውን ጋዜጣዊ መግለጫዎች እና ትንተናዎች በማሰባሰብ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች የመሰነድ ስራ ተሰርቷል።

## *2.2 የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ክትትል እና ምርመራ*

**የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ምርመራ ስራ**

በዋናው መ/ቤትና በስምንቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ከ2013 በጀት አመት ሶስተኛው ሩብ አመት ወደ 2013 በጀት አመት አራተኛው ሩብ አመት የተሸጋገሩ 27 አቤቱታዎችን ጨምሮ በ2013 በጀት አመት አስራ አንድ ወራት በድምሩ 1933 አቤቱታዎች።

ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል 1158 ጉዳዮች በወንዶች፣ 399 ጉዳዮች በሴቶች እንዲሁም 376 ጉዳዮች በቡድን የቀረቡ አቤቱታዎች ናቸው። ከእነዚህ አቤቱታዎች መካከል 967 የሚሆኑ ቅሬታዎች በፌዴራልና ክልል ምክር ቤቶች ወይም በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ እንዲሁም ከያዟቸው ፍሬ-ጭብጦች አኳያ በሌሎች ተቋማት ስልጣን ስር የሚወድቁ በመሆናቸው በኮሚሽኑ በቀጥታ አልተስተናገዱም። ከእነዚህ በቀጥታ ካልተስተናገዱ ማመልከቻዎች መካከል ለ804 አቤቱታ አቅራቢዎች የሕግ ምክር እና አስተዳደራዊ መፍትሄ ምክረ ሀሳብ ተሰጥቷቸዋል። ቀሪዎቹ 163 አቤቱታዎች ደግሞ ጉዳዮቹ ወደሚመለከቷቸው አስፈጻሚ አካላት ተመርተዋል።

ከነዚህም ውስጥ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ከቀረቡ አቤቱታዎች ውስጥ:-

- ቀርሳ ወረዳ ጥቁር አቡሎ እና ኪቲምቢሌ ቀበሌ የሕግ ታራሚ ቤተሰቦችን ከቤት ንብረታቸው በማፈናቀል እና ንብረታቸውን ሙሉ በሙሉ ማውደም፤
- የጨራ ወረዳ ቁምባቤ ከተማ ቀበሌ ነዋሪዎች በቀበሌያቸው በሚገኘው የቡና መፈልፈያ እና ማበጠሪያ በሚለቀቀው ተረፈ-ምርት በአካባቢው ነዋሪዎች በንጹህ እና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብታቸውን የሚጥስ ተግባር፤
- ከጂማ ዞን ሊሙ-ኮሳ ወረዳ ሊሙ ከተማ ቀበሌ እና በበደሌ ከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦች በወረዳው ፖሊስ አባል በደረሰባቸው ድብደባ የአካል ጉዳት መድረስን በመመርኮዝ የቀረቡ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ የቀረቡትን አቤቱታዎች መሰረት በማድረግ ምርመራ ተደርጎ የመፍትሄ ሀሳብ ለሚመለከታቸው አካላት ቀርቧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተከሰተው የሰላምና ጸጥታ መደፍረስ የደረሰውን መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በሚመለከት በ40 የኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎች ምርመራ ተካሂዷል፡፡ የምርመራ ስራው እንደተጠናቀቀ የመጀመሪያ ሪፖርት ተዘጋጅቶ አፋጣኝ ትኩረትና እርምጃ ያስፈልጋቸዋል ተብለው የተለዩ ጉዳዮችን በሚመለከት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካሎች ምክረ ሃሣብ የተሰጠ ሲሆን፣ ኮሚሽኑ ሪፖርቱን ይፋ ባደረገበት ጋዜጣዊ መግለጫ ግኝቶቹን ለህዝብ ይፋ ተደርገዋል፡፡

በዋና መ/ቤት ምርመራ የተደረገባቸው አቤቱታዎች የሚከተሉት ናቸው:-

- በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን ዶቤ ክስታኔ ማህበረሰብ ተወካዮች ያቀረቡት አቤቱታ፤
- በድቡብ ክልል በጉራጌ ዞን እንሞርና ኤነር ወረዳ ማህበረሶች ከወረዳ ጥያቄ ጋር በተያያዘ የመብቶች ጥሰቶች ደርሰውብናል በሚል ያቀረቡት አቤቱታ፤
- በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ወሊሶ ከተማ  ከአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ጋር በተያያዘ በአማራ ብሄር ተወላጆች ላይ ደርሶ በነበረው ጉዳት የተደረገውን ምርመራ በመንተራስ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን መልሶ ከማቋቋምና ድጋፍ መስጠት ጋር በተያያዘ ያቀረቡት ቅሬታ፤

- በአፋርና ሶማሌ ብሄራዊ ክልሎች አዋሳኝ ስፍራዎች ላይ በተነሳ ግጭት የደረሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት በተመለከተ፤
- በደቡብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በኮንሶ ዞን ሰገን ዙሪያ ወረዳና አሌ ልዩ ወረዳ እንደዚሁም በደራሼ ልዩ ወረዳ፤
- በኦሮሚያ ክልል በጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባብር እና ምስራቅ ወለጋ ዞኖች በተለያዩ ምክንያቶች ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሰዎችን ሁኔታ፤
- የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያዩ ታራሚዎች ላይ ከሰብአዊ አያያዝ እና ከአካል ደህንነት መብቶች ጋር በተገናኘ በታራሚዎች ለፍ/ቤት የቀረበው የሰብአዊ መብት ጥሰት አቤቱታ ኮሚሽኑ እንዲያጣራ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ምርመራ ተከናውኗል።

የሰብአዊ መብቶች ምርመራ ዳይሬክቶሬት በእቅዱ መሰረት ስራዎቹን ያከናወነ ቢሆንም በቂ የሆነ የሰው ኃይል ያለመኖር ከሚቀርቡ አቤቱታዎች አንጻር የተፋጠነ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ መሆኑ፣ የስራ ክፍሉ ቋሚ ሬጀስትራር ባለሙያ የሌለው በመሆኑ አቤቱታዎች በአግባቡ ለመለየት እና መዝገቦችን ለማደራጀት ያለመቻል፣ የሚቀርቡ አብዛኞቹ አቤቱታዎች በፍ/ቤት እየታዩ ያሉና የታዩ ጉዳይች በተደጋጋሚ መቅረብ እንዲሁም በኮሚሽኑ ስልጣንና ሃላፊነት ስር የማይወድቁ ጉዳዮች በተደጋጋሚ መምጣት ባለሙያዎች ላይ የስራ ጫና ፈጥሯል። እነዚህንም ተግዳሮቶች ለመፍታት ያስችል ዘንድ አዲሱ የኮሚሽኑ የመዋቅር ጥናት ይህንን ግንዛቤ ውስጥ እንዲከት ተደርጓል።

**የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ የተደረጉ የክትትልና ማማከር ስራዎች**

**በኮሚሽኑ አማካኝነት በሚከተሉት የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮችላይ ክትትል ተከናውኗል፡፡**

1. የታራሚዎች እና የተጠርጣሪዎች ሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ በተመለከተ
    - በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ሥር የሚገኙ 3 ማረሚያ ቤቶች (ዝዋይ ማረሚያ ተቋም፤ ሸዋ ሮቢት ተሃድሶ ማዕከል እና ድሬዳዋ ማ/ቤት) እና በሰባት ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ክትትል ተደርጎ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ምክረ-ሃሳቦች ተሰጥተዋል።
    - በአማራ ክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ሥር የሚገኙ 9 ማረሚያ ቤቶች (ቢቸና፤ ሰቆጣ፤ ላሊበላ፤ ሞጣ፤ ዳባት፤ ደብረ ታቦር፤ ደባርቅ፤ ባህር ዳር ማ/ቤቶች) እንዲሁም በባህር ዳር

ቅ/ጽ/ቤት አማካኝነት በ18 ማረሚያ ቤቶች፣ በአሶሳ ዞን ስር በሚገኙ 5 ወረዳዎች እና 2 የከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጣቢያዎች እና በሁለት የአገር ውስጥ ተፈናቃይ ካምፖች ላይ የሰብአዊ እርዳታ እና የተፈናቃዮችን አያያዝ በተመለከተ ክትትል ተደርጓል። በተመሳሳይ የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተ በባለድርሻ አካላት አተገባበር ላይ የተደረገውን የክትትል ግኝት መነሻ በማድረግ ክትትል ለተደረገባቸው ተቋማት ግብረ መልስ (ምክረ-ሃሳብ) የተሰጠ ሲሆን ክትትል የተደረገባቸው ተቋማትም የሜጫ፣ ደ/አቸፈር ወረዳዎችና የክልል ምክር ቤት ጤና እና ትምህርት ቢሮ እና በሁለቱ የወረዳ ከተሞች እና ባህር ዳር ከተማ የሚገኙ 6 የግልና የመንግሥት ት/ቤቶች ናቸው። በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የኮሮና ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊትና በኋላ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ለመከታተል በታቀደዉ መሰረት በአዊ ብሔረሰብ ዞንና በደቡብ ጎንደር ዞን በሚገኙ ሴቶችና ህጻናት ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ፣ ፍትህ መምሪያና ፖሊስ መምሪያ ላይ ክትትል ተደርጓል። እንዲሁም በማዕከላዊ ጐንደር ዞን ጐንደር ከተማ ኳራንታይን ላይ ያሉ ዜጎችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ በተመለከተ አንድ ጊዜ የክትትል ስራ ለመስራት ታቅዶ ተከናውኗል።

- በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ 11 ፖሊስ ጣቢያዎችና የተጠርጣሪዎች ማቆያ (ሰንዳፋ፣ ለገጣፎ፣ ዱከም፣ ቢሾፍቱ፣ ዴራ፤ ገላን፣ ሰበታ፣ ቡራዩ፣ ሞጆ፤ አርሲ ነገሌ፤ ጭሮ) በቁጥጥር ስር የዋሉ ተጠርጣሪዎችን አያያዝ ሁኔታ፤
- በአዳማ ማረሚያ ቤት የሚገኙ ታራሚዎች ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ለመከላከል/ለመጠበቅ የተወሰዱ እርምጃዎች እና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ፤
- በአፋር ክልል በሚገኙ 5 ማረሚያ ቤቶች (በቂልበቲ ረሱ ማረሚያ ቤት፤ በአውሲ ረሱ ማረሚያ ቤት፤ በገቢ ረሱ ማረሚያ ቤት፤ በፈንቲ ረሱ ማረሚያ ቤት፤ በሀሪ ረሱ ማረሚያ ቤት) እንዲሁም በሎጊያ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ፤ ሚሌ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ፤ ሰመራ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ፤ አሳይታ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ፤ ዱብቲ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ፤ ጐሊና ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ፤

- በደ/ብ/ብ/ህ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር በሚገኙ በቦንጋ፣ በሚዛን፣ በማሻ፣ በቴፒ እና በሳጃ ማረሚያ ተቋማት እንዲሁም በዱራሜ፣ ቡታጅራ፣ ሀላባ፣ ሆሳዕና፣ ወላይታ፣ ተርጫ  ወልቂጤ እና ወራቤ ላይ በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች፤
- በጂግጂጋ ቅ/ጽ/ቤት ወቅታዊ በ 3 ፖሊስ ጣቢያ ላይ እና 1 ስደተኛ ጣቢያ ላይ ክትትልና በተጨማሪም በሀቫና ተጠርጣሪ ማቆያ፣ በፋፈም ማረሚያ ቤት እና በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 ማረሚያ ቤት ላይ ክትትል ተደርጎ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ምክረ ሀሳቦች ተሰጥተዋል። ከዚህም በተጨማሪ እ.ኤ.አ. 2020 የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቀንን አስመልክቶ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ቤት የአስተዳደር አካላትና ሰራተኞች በሰብአዊ መብት እና በሕግ ታራሚዎች አያያዝ ዙሪያ የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል። በስልጠናው የሴት ታራሚዎች አያያዝና ከእስራት ውጭ የሚወሰዱ እርምት እርምጃዎች ላይ ጽሑፍ በማዘጋጀት ገለጻ ተደርጓል።
- በጋምቤላ ክልል በሚገኙት አራት ማረሚያ ቤቶች ላይ ክትትል በማድረግ በተገኙ ክፍተቶች ዙሪያ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት መግባባት ላይ የተደረሰ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ በኑዌር ዞን ማረሚያ ቤት በወቅታዊ የሃገር አለመረጋጋት ጉዳይ ተጠርጥረው በማረሚያ ቤት የሚገኙ አስራ አንድ ተጠርጣሪዎች በተደረገው ውይይት ሊፈቱ ችለዋል። በተጨማሪም ጋምቤላ ከተማን አካቶ በአምስት ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን በአቦቦ ወረዳ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የነበሩ ሶስት ተጠርጣሪዎች በተደረገ ክትትል እንዲፈቱ ተደርጓል።
- በጋምቤላ ከተማና በሶስቱ የዞን ማረሚያ ቤቶች ውስጥ በወቅታዊ የሃገር አለመረጋጋት ጉዳይ ተጠርጥረው በማረሚያ ቤት የሚገኙ ተጠርጣሪዎች በተደረገው ውይይት ከጋምቤላ ማረሚያ ቤት 39 ሰዎች፣ ከአኝዋክ ዞን ማረሚያ ቤት 18 ሰዎች መፈታት ችለዋል። እንዲሁም በክልሉ በሚገኙት በ4ቱም ማረምያ ቤቶችና በ11 ወረዳዎች የሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ የታራሚዎችና የተጠርጣሪዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ ክትትል ለማድረግ ተችሏል።
- በጂማ ቅ/ጽ/ቤት በ9 የዞን ከተሞች እና 18 ወረዳዎች ባሉት የፖሊስ ጣቢያዎችና ማቆያዎች ፖሊስ ጣቢያዎች በተለያዩ ወንጀሎች ተጠረጥረው በሕግ ቁጥጥር ስር ያሉ

ሰዎች አያያዝ ላይ ክትትል በማድረግ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ግብረ-መልስ የተሰጠበት ከመሆኑም በላይ በርካታ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ተደርጓል። ለምሳሌ፡- ከሕግ አግባብ ውጪ የታሰሩ ሰዎች ወዲያውኑ እንዲለቀቁ መደረጉ እና አስቸኳይ ህክምና ማግኘት ያለባቸው ሰዎች ወደ ጤና ተቋም እንዲወሰዱ የተደረገውን መጥቀስ ይቻላል። ከምስራቅ እና ምእራብ ሐረርጌ ዞኖች በሰፈራ የመጡ ሰዎች የሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ ኮሚሽኑ ባደረገው በራስ ተነሳሽነት ምርመራ መሠረት የተሰጠውን የመፍትሄ ሃሳብ አፈጻጸም ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ግብርና እና ተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ቢሮ ተፈናቃዮችን በተዘጋጀላቸው ስፍዎች ለማስፈር ኮንትራት የተሰጠ መሰረተ ልማት ባለመጠናቀቁ ምክንያት የዘገየ ሲሆን በዴዴሳ ወረዳ የምበሮ እና ዴዴሳ ያሉ ሰዎች ተራ በተራ ለማንሳት የመጓጓዣ ጨረታ የማውጣት ሂደት ላይ ስለመሆናቸው በክትትል ተለይቷል።

- በጅማ ከተማ ፖሊስ ጣቢያዎች ላይ በተደረገ ክትትል የወንጀል ተግባር የተፈጸመባቸው ህጻናት በማቆያ እጥረት ምክንያት ከተጠርጣሪዎች ጋር ፖሊስ ጣቢያ እንዲቆዩ መደረጉ ስህተት እና የመብት ጥሰት በመሆኑ እንዲታረም የተሰጠ ግብረ መልስ በጅማ ከተማ ሁለቱም ፖሊስ ጣያዎች ተግባራዊ ሆኖ ወንጀል የተፈጸመባቸው ህፃናት በአማራጭነት በቤተዘመድ ዘንድ የሚቆዩበት ስርአት ተፈጥሯዋል።
- በአሶሳ ዞን እና ከማሺ ዞን ማረሚያ ቤቶች የሕግ ታራሚዎችን አያያዝ በሚመለከት ክትትል ተደርጎ በተለዩ ችግሮች ላይ ማስተካከያ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው አካላት ምክረ-ሃሳብ ቀርቧል። በክትትሉ በዋነኝነት በማረሚያ ቤቶች ያለፍርድ በቀጠሮ ታስረው ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ ሰዎች ችግር የተስተዋለ ሲሆን በሂደቱም ችግሩ እንዲፈታ ጥረት ተደርጓል። በማረሚያ ቤቶች ያለው ሰብአዊ መብቶች አያያዝ እንዲሻሻል እና ከኮቪድ 19 በሽታ ጋር በተያያዘ ታራሚዎች ተጋላጭ እንዳይሆኑ በክትትሉ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተከናውኗል። በተጨማሪም የተጠርጣሪዎችን ሰብአዊ መብቶች አያያዝ በሚመለከት በአሶሳ ዞን ውስጥ ባሉ 8 የወረዳ ፖሊስ ጣቢያዎች እና 2 የከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጣቢያ ማቆያዎች ምክረ-ሃሳብ ተሰጥቷል። የማማከር ስራዎችም ተሰርቷል።

2. በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያየዩ አካባቢዎች የሚገኙ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሰብአዊ መብቶች አያያዝን በተመለከተ ኮሚሽኑ ከተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ቢሮ ጋር በመተባበር ለማድረግ ካቀዳቸው የክትትል ስራዎች መካከል ሶማሌ ክልል የሚገኙ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች ላይ የመጀመሪያ ዙር ክትትሉን አካሂዷል፡፡ ክትትሉ ስድስት ቦታዎችን የሸፈነ ሲሆን እነዚህም፡-

- በሶማሌ ክልል ፋፈን ዞን ባቢሌ ወረዳ የሚገኙ የቆለጂ የተፈናቃዮች ካምፕ፣ በቱሊጉሌድ ወረዳ የሚገኙ ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው የተመለሱ የበፊት ተፈናቃዮች መኖሪያ እና በጎልጃኖ ወረዳ አዲስ የሰፈሩ የበፊት ተፈናቃዮች መኖሪያ፤ እንዲሁም
- ከሲቲ ዞን ኤረር ወረዳ ቀለሜ ቀበሌ የሚገኙ ተፈናቃዮች፣ መጋላ አድ ቀበሌ የሚገኙ አዲስ የሰፈሩ የበፊት ተፈናቃዮች መኖሪያ እና በድሬዳዋ ከተማ የሱማሌ ክልል ተፈናቃዮች በጊዜያዊነት ተጠልለው የሚገኙበት የሚሊንየም ፓርክ ናቸው፡፡

በጉብኝቱ ወቅት ከተፈናቃዮች እና ሌሎች ዘላቂ መፍትሄ የተሰጣቸው የበፊት ተፈናቃዮች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ኃላፊዎችና ሰራተኞችን እና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን በማነጋገር መረጃዎችን በመሰብሰብ ለሚመከለታቸው አካላት ምክረ ሃሳቦችን ለመስጠት የክትትሉን ሪፖርት ለማጠናከር ተችላል፡፡

3. ከጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ኦነግ ሸኔ ተብሎ የሚታወቀው ቡድን ከሚንቀሳቀስባቸው ቦታዎች (ምዕራብ ወለጋ ሙጊ ወረዳ ተብሎ ከሚጠራ አካባቢ ካሉ 3 ቀበሌዎች - የነቼ፣ ጎቢና ሸበል) ወደ ጋምቤላ ከተማ የተፈናቀሉ ሰዎችን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታን ተመልክቶ ከጋምቤላ ክልል ከፍተኛ ሃላፊዎች ጋር ውይይት አድርጎ የመፍትሔ እርምጃዎች ላይ ተወያይቷል፡፡

4. በትግራይ ክልል የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ በብሔር ማንነታቸው ተጠርጥረው የተያዙ የትግራይ ተወላጆች እንዲሁም ጋዜጠኞች በሚገኙባቸው በአዲስ አበባ ከተማ የተመረጡ አምስት ፖሊስ ጣቢያዎች በወቅቱ በመገኘት በአያያዝ ሁኔታቸው ላይ የሰብአዊ መብት ክትትል ስራ ተከናውኗል፡፡

5. ከወቅታዊ የሃገር አለመረጋጋት ጉዳይ ጋር ተያይዞ ክትትል ከሚፈልጉ ጉዳዮች መካከል የመቱ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ከመደበኛ ፖሊስ ጣቢያዎች ውጪ መታሰራቸው በቀረበ ጥቆማ

መሰረት የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ክትትል ቡድን በመቱ ከተማ እና በኢሉአባቦር ዞን ፖሊስ መምሪያ በመገኘት በጉዳዩ ላይ ውይይት በማድረግ የመቱ ዩኒቨርሲቲ መምህራንን ጨምሮ 20 ግለሰቦች በኮማድ ፖስት ትዕዛዝ ከመደበኛ ፖሊስ ጽ/ቤቶች ውጪ ቀርሳ በሚባል ቦታ ስለመታሰራቸው ተረጋግጦ በክትትል ሂደቱ በተሰራ ስራ የመቱ ዩኒቨርሲቲ መምህራንን ጨምሮ 17ቱ ሰዎች እንዲፈቱ ሲደረግ የተቀሩት ሶስት ተጠርጣሪዎች ወደ መደበኛ ፖሊስ ጣቢያ እንዲሄዱ ተደርጓል።

6. ከአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ተከትሎ ከተፈጠር ችግር ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት እየታዩ ያሉ ጉዳዮች ላይ ክትትል ለማድረግ በታቀደው መሠረት በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ተዘዋዋሪ ችሎት ሲያስችል የነበረውን የወንጀል ችሎት ላይ በመገኘት ክትትል ተደርጎ በክትትሉ በታዩ እና ፍትህ የማግኘት መብትን በሚጥሱ ጉዳዮች ላይ ከፍርድ ቤት እና ከዓቃቤ ሕግ ጋር ውይይት በማድረግ ችግሮቹ እንዲታረሙ ተደርጓል።

7. በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ምረቃ ፕሮግራም ላይ 'ጃዋር መሐመድ ይፈታ፣ ፍትህ ለሃጫሉ፣ ሁሉም የፖለቲካ እስራኞች ይፈቱ' በማለት ተቃውሞ በማሰማቱ በጅማ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ተይዞ የነበረውን የመሐመድ ዴኪስሶ እና ሶስት ተጠርጣሪዎች ጉዳይ በቀረቡበት ሁለቱ ክሶች ጋር ተያይዞ የጊዜ ቀጠሮ ክርክር ላይ ክትትል ተደርጎ በሂደቱም በታዩ ክፍተቶች ላይ ከጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ጋር ውይይት ተደርጎ ጉዳዮቹ እንዲስተካከሉ ተደርጎ የዋስትና መብቱ እንዲከበር ተደርጓል። በፖሊስ ጣቢያ ቆይታ ጊዜውም በተደጋጋሚ ፖሊስ ጣቢያ በመገኘት ክትትል ተደርጓል።

8. በአዳማ ከተማ ከኦሮሚያ ክልል 13 ዞኖች የተውጣጡ 29 አመራሮች በተገኙበት በኦሮሚያ ክልል እየተስተዋለ ስላለው የፍትህ መጓደል እና እያስከተለ ባለው የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ዙሪያ ምክክር ተደርጓል። በምክክር መድረኩም አንዳንድ የተቃዋሚ ፓረቲ አባል የሆኑ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉ ተጠርጣሪዎች በፍርድ ቤት ጥፋተኝነታቸው ሳይረጋገጥባቸው ጠላት ናቸው ተብለው እንደሚፈረጁ፤ በፍርድ ቤት የዋስትና መብት እንዲከበርላቸው ቢወሰንም ፖሊስ ውሳኔውን እንደማይተገብር፤ ተጠርጣሪዎች እጅግ ጠባብ በሆነ ክፍል ውስጥ ብዙ ሆነው መታሰር፤ ታመው ወደ ህክምና ለመሄድ ሲጠይቁ ለፖሊስ አበል እንዲከፍሉ እንደሚጠየቁ እና ድብደባ እንደሚደርስባቸው ለኮሚሽኑ አቤቱታ

እንደሚደርሰው በምክክር መድረኩ ለተሳተፉት ተገልጿል። በውይይቱ ወቅት የተነሱትን ጉዳዮች ማዕከል በማድረግ በፖሊስ ጣቢያዎች ዳሰሳ በማድረግ ሊስተካከሉ በሚገቡ ክፍተቶች ላይ መስራት እንደሚገባ በውይይት መድረኩ መግባባት ላይ ተደርሷል።

9. በቀርሳ ወረዳ በጥቁር አቡሎ ቀበሌ ነዋሪ የነበሩ እነ ትጃኒ አ/ጂሃድ ተብለው የሚጠሩ አመልካቾች ጉዳይ በኢሰመኮ ምርመራ ውስጥ በተቀመጠው የመፍትሄ ሃሳብ እና በተደረገው የአፈጻጸም ክትትል ከቀያቸው ተፈናቅለው የነበሩ 42 ሰዎች ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል።

10. በ2013 በጀት ዓመት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል የፍርድ ቤት ክስ ሂደትን ከሰብአዊ መብቶች አንፃር የመከታተል ስራ መጀመሩ ነው። በዚህም የቅድመ ክስ እንዲሁም የክስ ሂደቶችን ባለሙያዎች በፍርድ ቤት በመገኘት ተከታትለው መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን፤ ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ ተሰጥቷል፣ እንደአስፈላጊነቱ መግለጫዎች እንዲወጡ ተደርጓል። ከነዚህም ውስጥ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በኦሮሚያ በተለያዩ ዞኖች፤ ወረዳዎች እና ከተሞች ላይ ተፈጥሮ በነበረው ሁከት እና ግርግር ምክንያት በሰው ህይወት እና በንብረት ላይ በደረሰው ጉዳት በወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ከዋሉ እና ክስ ተመሰርቶባቸው በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምዕራብ ምድብ ተዘዋዋሪ ችሎት (ጅማ) እየተመላለሱ የነበሩትን ተጠርጣሪዎች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት እና ሀገራችን በፈረመቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች መሠረት ክስ የቀረበባቸው ሰዎች መብትን በተመለከተ ያለውን ሁኔታ ለመከታተል በ8 የፍ/ቤት ቀጠሮዎች በመገኘት የክስ ሂደቱን በተመለከተ ክትትል ተደርጓል። በክትትል ሂደቱ የተለዩ ክፍተቶችን በተመለከተ ከተከሳሽ ጠበቆች፣ ከተከላካይ ጠበቆች እንዲሁም የተከሳሽ ንብረቶችን በተመለከተ መፍትሄ የሚገኝበት መንገድ ላይ ውይይት ተደርጓል። በዚህም መሰረት ተከሳሾች በአደራ የተቀመጡ ንብረቶቻቸውን በቤተሰቦቻቸው ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻቸው በኩል ከፖሊስ ጣቢያ መውሰድ እንደሚችሉና በአደራ ያልተቀመጡ በፖሊስ እጅ የሚገኙ ንብረቶች ደግሞ እንዲጣሩ ለፖሊስ ምክረ ሀሰብ ተሰጥቷል።

11. በመንግስት የሚወጡ ሕጎች ከሕገ መንግስቱ እንዲሁም ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ከማረጋገጥ አኳያ ረቂቅ የወንጀል

ሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጉን በመፈተሽ እና መሻሻል ያለባቸውን አንቀጾች በመለየት ምክረ ሃሣቦችን የያዘ ባለ 33 ገጽ ሪፖርት አዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው አካላት እና ከተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚሰሩ የሲቪክ ማህበራት ጋር የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ አስተያየት ካሰባሰበ በኋላ ሪፖርቱን ለሚመለከታቸው አካላት አቅረቧል።

12. በሰብአዊ መብቶች የድርጊት ረቂቅ መርሃ ግብር ላይ የባለሙያ አስተያየት ተሰጥቷል።

13. ኢሰመኮ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38 ላይ በተደነገጉ መለኪያዎች/መመዘኛዎች ላይ ተመስርቶ የመምረጥና የመመረጥ መብትና ሌሎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች መከበራቸውን፣ መጠበቃቸውን እና መሟላታቸውን ክትትል አድርጓል። በመሆኑም በምርጫው ሁደት የቅድመ ምርጫ ምዕራፍ አካል በሆነው የመራጮች ምዝገባ ሂደት ላይ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ለማካሄድ ይረዳ ዘንድ የክትትሉ ማስፈጸሚያ ቢጋርና የምርጫ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ቀርጿል።

    የምርጫው ሂደት የሚመራበትን የሕግ ማዕቀፎች (አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪዎች) በተመለከተ በኮሚሽኑ ለምርጫ ክትትል ተግባር ለተመረጡ የዋና መ/ቤት እና የቅ/ጽ/ቤት ሞያተኞች በክትትሉ ላይ በአግባቡ እንዲሳተፉ ለማድረግ የ3 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል። በክትትሉ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ሊያነጋግሯቸው የሚገቡ 6 የባለድርሻ አካላትን ለይቷል፣ የመረጃ አሰባሰብ እና የስነ-ምግባር መመሪያዎችን አዘጋጅቷል። ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ 6 አይነት ቼክሊስቶችን (ለመራጮች የተዘጋጀ ቅፅ፤ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተዘጋጀ ቅፅ፤ ለጸጥታ አካላት የተዘጋጀ ቅፅ፤ የምልከታ መረጃ መሙያ ቅፅ፤ ለምርጫ አስፈጻሚዎች የተዘጋጀ ቅፅ፤ በየደረጃው ለሚገኙ አስተዳዳሪዎች የተዘጋጀ ቅፅ) የክትትል መርህና ሙያን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል።

    ከዚህም በተጨማሪ ‘ምርጫ እና ሰብአዊ መብቶች’ የሚል ስልጠና ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) እና ከከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት (ኢሰመድህ) ጋር በመተባበር ከሲቪል ማህበራት ለተውጣጡ በባህር ዳር (ለ25 ተሳታፊዎች) እና በሃዋሳ (ለ28 ተሳታፊዎች) የሁለት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል።

14. 6ኛው ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫ በተመለከተ

- በ6ኛው ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫ ላይ የቅድመ ምርጫ ዋና ዋና ሂደቶች የሆኑትን የመራጮች ምዝገባን እና የምርጫ ቅስቀሳ ሂደት ላይ ክትትል ለማድረግ በክትትል ስራ ላይ ለሚሰማሩ የዋና መ/ቤት እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሞያተኞች የ3 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠናው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38 እንዲሁም በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ላይ በተደነገጉ መለኪያዎች/መመዘኛዎች ላይ ተመስርቶ የመምረጥና የመመረጥ መብትና ሌሎች የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች በተመለከተ ዝርዝር የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል።

- በ6ኛው ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫ ላይ የቅድመ ምርጫ ዋና ዋና ሂደቶች የሆኑትን የመራጮች ምዝገባን እና የምርጫ ቅስቀሳ ሂደት ለመከታተል የክትትል ዕቅድና አፈፃፀም አቅጣጫ (strategy)፤ የስነ-ምግባር መመርያ እና ልዩ ልዩ የመስሪያ እንዲኬተሮች የምርጫውን የሕግ ማዕቀፍና የክትትል መርህን መሰረት በማድረግ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

- ኢሰመኮ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38 ላይ በተደነገጉ መለኪያዎች/መመዘኛዎች ላይ ተመስርቶ የመምረጥና የመመረጥ መብቶች መከበራቸውን በተመለከተ ክትትል አድርጓል። በዚሁ መሰረት በ6ኛው ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ምርጫ ላይ የቅድመ ምርጫ ዋና ዋና ሂደቶች የሆኑትን የመራጮች ምዝገባን እና የምርጫ ቅስቀሳ ሂደት ላይ መሠረታዊ የክትትል መርሆዎችን በመከተል ክትትል አካሂዷል።

- ኮሚሽኑ ለሚያካሂደው የቅድመ ምርጫ ክትትል ስራ በአጠቃላይ 32 ባለሙያዎችን የያዘ 16 ቡድኖችን አዋቅሮ (አንድ ቡድን በውስጡ የቡድን አስተባባሪ እና አንድ ባለሙያ ይዟል) እያንዳንዱ ቡድን በ40 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ክትትል አድጓል። በዚሁ መሰረት ክትትሉ የተካሔደው ዝርዝር የክትትል ቼክሊስቶችን/መጠይቆችን በማዘጋጀት ምርጫው ወደሚካሄድባቸው አካባቢዎች አሰማርቶ ለሚመለከታቸው የምርጫ አስፈጻሚዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ በምርጫ ጣቢያዎች ላይ ምልከታ በማድረግ እና የሚመለከታቸው የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችን/ ተወካዮችን በማነጋገር ነው።

- በምርጫ የሕግ ማዕቀፎች ዙሪያ ለፖሊስ፤ ለጸጥታ ዘርፍ ኃላፊዎችና ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተቋማት ባለሙያዎች እና አመራሮች ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል የ2 ቀናት የአሰልጣኖች ስልጠና ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ባለሞያዎች ተሰጥቷል። በዚህ ሥልጠና ላይ በዋናነት በምርጫ ወቅት ሰብአዊ መብቶችን በማስከበር ረገድ የጸጥታው ዘርፍ፤ የዓቃቤ ሕግ፣ የፖሊስ ተቋማት አመራሮች እና ባለሙያዎች ሚና ተዳሰዋል።

- ይህን ስልጠና በአግባቡ ተደራሽ ለማድረግ በባለሞያ በተዘጋጀው የማሰልጠኛ ሰነድና የምርጫ ዕለትን ከሰብአዊ መብቶች አንጻር ለመከታተል የሚያስችል ወጥ የሆነ መረጃ ለመሰብሰቢያነት የሚገለግሉ የቃለ መጠይቆችና የምልከታ ቼክሊስቶችና ሪፖርት አደራረግ ላይ ጥልቀት ያለው ውይይት በማድረግ ሰነዱና ቼክሊስቱ እንዲዳብር ተደርጓል።
- ስልጠናውን የወሰዱ ባለሙያዎች ለክትትል፣ ሪፖርት ለማድረግ እና ለሎጂስቲክስ በሚያመች መልኩ ምደባ በማድረግ ዝርዝር የተግባርና የበጀት እቅድ እዲያዘጋጁ ተደርጓል።

15. በተለያዩ ወንጀሎች ተጠርጥረው በፖሊስ ጣቢያዎች ታስረው ያሉትን ለምሳሌ፡- የጂማ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሠራተኞች 10 ሰዎች ጉዳይ ላይ ክትትል ሲደረግ ቆይቶ የጂማ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በዋስ እንዲወጡ ካዘዘ በኋላ ፖሊስ ሳይለቃቸው ወደ ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ በማዛወር በእስር ላይ የሚገኙ ሲሆን በዋናው መስሪያ ቤታችን በኩል ክትትል እየተደረገባቸው ይገኛል። እንዲሁም የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ተማሪ የነበረው መሐመድ ዴኪስሶ ከጅማ ከተማ ወረዳ 1 ፖሊስ ጣቢያ ከተለቀቀ በኋላ ባልታወቁ የመንግስት ፀጥታ አካላት ተይዞ መሰወሩ በቤተሰቦቹ በኩል ጥቆማ ከደረሰን በኋላ ክትትል በማድረግ ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ በእስር ላይ የሚገኝ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።
16. በጅግጅጋ ቅርንጫፍ ከምርጫ ጋር በተገናኘ የቅድመ ምርጫ ክትትል ከሴቶች እና ህጻናት ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አስተባበሪ ጋር በመሆን የተከናወነ ሲሆን ክትትል የተከናወነባቸው በታዎችም ደገሀቡር፣ ቀብሪደሀር፣ ጅግጅጋ እና ሺንሌ ዞን ሲሆኑ በዚህም መሻሻል የሚገባቸው ተለይተው ሪፖርት ተደርጓል። በተጨማሪም የምርጫ ቅስቀሳ

ላይ ችግር እንደነበር እና የምርጫ ጣቢያዎች በወቅቱ ያለመከፈት በዋናነት የተለዩ ችግሮች ናቸው፡፡

17. በተመሳሳይ ከሶማሌ ክልል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ጋር በመሆን በጅጅጋ ማረሚያ ቤት ክትትል የተደረገ ሲሆን በዚህም የእስረኞች መብቶችነ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የታዩ ክፍተቶች እንዲስተካከሉ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በቀበሌ 04 ማረሚያ ቤት፣ ፋፈም ዞን ማረሚያ ቤት እና በሀቫና ማረሚያ ቤት በመገኘት የታራሚዎች እና የታሰሩ ሰዎች መብቶች አያያዝ በተመለከተ ክትትል ተደርጓል፡፡ በዚህም በሀቫና ማረሚያ ቤት የንጽህና ጉድለት ያለበት በመሆኑ እንዲፀዳና በምግብ ወቅት ዳቦ ብቻ ይሰጣቸው የነበረ ሲሆን ምግባቸው እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

## *2.3 ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች*

በኮሚሽኑ የውስጥ አሰራርም ሆነ በሰብአዊ መብቶችን የማስፋፋት እና የማሰከበር ስራው ሥርዓተ-ጾታን በተገቢው መንገድ ለማካተት ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመተባበር የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት /ግምገማ ተሰርቶ የኦዲቱ ሪፖርትና የሥርዓተ-ፆታ ማካተቻ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ሥርዓተ-ፆታን በኮሚሽኑ ውስጥም ሆነ በሌሎች ተቋማት በአግባቡ መካተቱን መከታተልና የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚቻልበትን አማራጮች መጠቆም እንዲቻል የኮሚሽኑን ባለሙያዎች በሥርዓተ-ፆታ ማካተት በ2013 በጀት ዓመት በዋናው መስሪያ ቤትና በሃዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በመቀጠል በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይህንኑ ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የሴቶችና ሕፃናት ዳይሬክቶሬት በኮሚሽኑ ያሉ ሌሎች ዳይሬክቶሬቶችና ስራዎቻቸው ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መብቶች አካተው ማቀዳቸውን፣ መተግበራቸውንና ሪፖርት ማድረጋቸውን ተከታትሎ ግብር መልስ ተሰጥቷል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ በኩል በኮሚሽኑ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማምጣት የሚያስችል የሴቶችንና የልጃገረዶችን መብቶች በተለየ ሁኔታ ለማስፋፋት፣ ለማስጠበቅ እንዲሁም ጥሰቶች ተፈጽመው ከተገኙ መፍትሔ የሚወሰድበትን አማራጮች የሚያመላክቱ ልዩ ፕሮጀክቶች ቀርፆእየሰራ ሲሆን በሌላ በኩል በኮሚሽኑ የሚሰሩ ስራዎች ሁሉ እንዲሁም የኮሚሽኑ የሰራተኞች ቅጥርና የሰው ሃብት አስተዳደር ሥርዓተ-ፆታን ያካተተ እንዲሆን ሁኔታዎችን እያመቻቸ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የኮሚሽኑ

የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አቤቱታ አቀባበልና ምርመራን በተመለከተ ቅበላው፣ ምርመራው እንዲሁም መስተንግዶው ሥርዓተ-ፆታን፣ ህፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን በአግባቡ ያካተተ መሆኑን በመፈተሽ አስፈላጊው ማሻሻያ እንዲደረግ የሚያስችል ስራ ጀምሯል። በሌላ በኩል ጨቅላ ሕፃን ያላቸው የኮሚሽኑ ሴት ባለሙያዎች ለስልጠና መንቀሳቀስ ሲኖርባቸው ጨቅላ ህፃኑ ለረጅም ጊዜ ከእናቱ እንዳይለይ አስፈላጊውን በጀት በመያዝ የጠባቂና የህፃኑን ወጪ በመሸፈን ሴት ባለሙያዎች በስልጠናና ስራቸው ካለምንም ስጋት እንዲሳተፉ፣ ሙያቸውን እንዲያዳብሩ ሁኔታውን እያመቻቸ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ የፀረ ወሲባዊ ትንኮሳና የስራ ቦታ ሥነ-ምግባር ፖሊሲ እና የወሲባዊ ትንኮሳ አቤቱታ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ረቂቅ ሰነድ እያዘጋጀ ሲሆን የመጀመሪያ ረቂቁ ተዘጋጅቶ ግብዓት ተሰብስቦ እየተጠናቀቁ ሲሆን በ2014 የበጀት ዓመት የኮሚሽኑ ሰራተኞችን በሙሉ ለማሰልጠን ዕቅድ ተይዟል።

**በሴቶች የፖለቲካ እና የምርጫ ተሳትፎ ሒደት የሚፈጸሙ ጥቃቶችን** እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ለመለየት የሚያስችል ሶስት ክልሎች እና አዲስ አበባ ከተማን ያካተተ ፈጣን የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል። በጥናቱም ላይ ግብዓት ለመሰብሰብ የካቲት 26 ቀን የግምገማ መድረክ 3 ወንድ እና 13 ሴት ተሳታፊዎች በተገኙበት ተካሂዷል። የጥናቱ የመጀመሪያ ረቂቅ እንደተዘጋጀ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ 5 ወንድ እና 15 ሴት ተሳታፊዎች በተገኙበት የውይይት መድረክ ተዘጋጅቶ ግብአት ተሰብስቧል። የዚህን ጥናት ግኝቶች እና ሌሎች መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የሴቶች የፖለቲካና የምርጫ ተሳትፎን የተሻለ ለማድረግ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ፣ የግንዛቤ መስጫና የግፊት ሥራዎች ተሰርቷል። ከነዚህም ውስጥ፥

- ሴቶች በፖለቲካ እና በምርጫ ተሳትፎ ሂደት ውስጥ የሚፈፀሙ ጥቃቶች እና ለሚፈፀመው ጥቃት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ስልቶችን ኮሚሽኑ ለይቷል። ይህንን ግብአት በመጠቀም የሴቶች በምርጫው ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል የክትትል ምልከታ ማዕቀፎችና የአፈፃፀም ዘዴዎች ዙሪያ እንዲሁም በክትትል ምልከታ መዕቀፎች አፈፃፀም ዙሪያ ላይ ስርዓተ-ፆታ ታሳቢ እንዲደረግ ለኮሚሽኑ ባለሙያዎች፣የሲቪል ማህበራት፤

ድርጅቶችና የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል። በዚህ ስልጠና በአራት ተከታታይ መድረኮች 40 ሴቶችና 41 ወንዶች ተሳታፊ ሆኖዋል።

- የሴቶችን የምርጫ ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል ማዕቀፎችና የአፈፃፀም ዘዴዎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረክ ተዘጋጅቶ በውይይቱ የተሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሲቪል ማህበራት ሴቶች በምርጫ እንዳይሳተፉ የሚያደርጓቸውን ችግሮች መለየት ችለዋል። ከችግሮቹ አንዱ እና ዋናው ጾታዊ ጥቃት እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዷል። 6ኛው አገር አቀፍ የምርጫ ሒደት ሥርዓተ-ጾታን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን የመከታተል አቅም ለማዳበር የኮሚሽኑ ባለሙያዎች፤ የሲቪል ማህበራት፤ ድርጅቶችና የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቅም ማሳደግ ተችሏል። በሶስት ዙር በተካሄዱት የስልጠና መድረኮች 32 ወንድ 16 ሴት ተሳታፊዎች አቅም መገንባት ተችሏል። በተጨማሪ በምርጫ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል፣ መለየትና ምላሽ መስጠትን አስመልክቶ ከተለያዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ 12 ሴት 18 ወንድ ተሳታፊዎች የሶስት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል።

## በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካ መስኮች ሥርዓተ-ፆታ ማካተትን፣ ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር እና በአፈፃፀም ረገድ ሴቶች ተጠቃሚነታቸውን እና ተሳታፊነታቸውን ማረጋገጥን በተመለከተ

በሰመራ (ዱብቲ፣ አሳይታ፣ አፋምቦ)፤ በአሶሳ (በመተከል ዞን ፓዊ/አልሙ፣ ማንዱራ፣ ግልገል በለስ እንዲሁም በአሶሳ ዞን አሶሳ ሆስፒታል፣ በሆሞሻ፣ መንጌ፣ ኩምሩክ፣ ሸርቆሌ፣ ባምባሴ)፤ በጅማ (በምስራቅ ወለጋ፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን እና በምስራቅ ሸዋ ዞኖች)፤ በተመረጡ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ላይ ክትትል ተደርጎ ምን እየተሰራ እንደሆነ፣ ያለው ጉደለት እና ጥንካሬ ተለይቶ ግብረ መልስ ተሰጥቷል። በተደረገው ክትትል በተወሰኑ ተቋማት ላይ የሴቶች ተጠቃሚነት እና ተሳታፊነት በተለያዩ መንገዶች እየተጠናከረ ያለ መሆኑን ኮሚሽኑ የተመለከተ ሲሆን ለምሳሌ በትምህርት እድል በተለያዩ ስልጠናዎች ቅድሚያ ለሴቶች እየተሰጠ ሲሆን በተወሰኑት ተቋማት ደግሞ ሴቶችን አካቶ በመስራቱ ዙሪያ እዚህ ግባ የሚባሉ ስራዎች እንዳልተሰራ እና ለወደፊቱ ግን በተጠናከረ መልኩ መሰራት እንዳለባቸው መግባባት ላይ ተደርሷል። በሌላ በኩል በክትትሉ ግኝቶች ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገው ውይይት አገልግሎት

የሚያጓትቱ ጤና ጣቢያዎች አገልግሎቱን በፍጥነት እና በተገቢዉ መንገድ እንዲሰጡ፣ ጾታዊ ጥቃት ደርሰባቸው የሚመጡ ሴቶችን የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጥ ማዕከል በሌለበት አካባቢዎች እንዲከፈት፣ ራምፕ (መንሸራተቻ) መንገድ በሌለባቸዉ ጤና ጣቢያዎች ራምፕ እንዲሰራ ማድረግ ተችሏል።

**የድጋፍና ክትትል ሥርዓት መዘርጋትን በተመለከተ ከኮሮና ቫይረስ አንፃር ለመብት ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እንድምታና ከጤና መብት አኳያ** እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችን በተመለከተ፡-

በፌዴራል ደረጃና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ ክፍለ ከተሞች እንዲሁም በኮሚሽኑ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (መቀሌ፤ ሀዋሳ፤ ባህር ዳር፣ ጅማ እና ጋምቤላ) አማካኝነት በክልል እና በዞን በሚገኙ በናሙናነት በተመረጡ ሆስፒታሎች፣ የጤና ጣቢያዎች እና የጤና ኬላዎች ላይ ክትትል ተካሂዶ ምክረ ሀሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት ተሰጥቷል። ከተሰጡት ምክረ ሃሳቦች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የእናቶች ቅድመ እና ድህረ ወሊድ ክትትል ከቀድሞው ጊዜ የቀነሰ መሆኑ እንዲሁም የሴቶች የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ለወረርሽኙ በሚሰጥ ትኩረት ሊስተጓጎል የማይገባው በመሆኑ ተገቢውን መረጃ ለሁሉም አካላት ተደራሽ ማድረግ እንደሚያስፈልግ፤
- ለህክምና የሚመጡ ተጠቃሚዎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ፤
- የኮቪድ-19 መለያና የሙቀት መለኪያ አለመኖሩን፣ ለጤና ባለሙያዎች ጭምር በቂ የሆነ የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛና ሳኒታይዘር አቅርቦት እንዲሁም የባለሙያዎች እና የመድሀኒት እጥረት መቀረፍ እንደሚገባው፤
- ቋሚ ክትትል ለሚያስፈልጋቸው እና ተላላፊ በሽታዎች ላለባቸው ታካሚዎች ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንደሚገባ የሚሉት ይገኙበታል።

**በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶች እና ትንኮሳዎች ዙርያ** በዋናው መ/ቤትና በሀዋሳ፣ ሰመራ፣ አሶሳ፣ ጅማ፣ ባህር ዳር

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት በተመረጡ ወረዳዎች ላይ በተለይ ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ጋር ተያይዞ ክትትል በማድረግ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ሴክተር ቢሮዎች፣ ህብረተሰቡን ከሚወክሉ ማህበራትና ተጽዕኖ ፈጣሪ አካላት ጋር ውይይት ተደርጓል። በተገኘው ውጤት የኮረና ቫይረስ መከሰቱን ተከትሎ ሴት ህጻናት ከትምህርት ገበታቸው በመቅረታቸው ጾታዊ ጥቃት፣ አካላዊ ጥቃት እና የጉልበት ብዝበዛ እየጨመረ መሆኑ፣ ባለግዴታ አካላት እና ማህበረሰቡ ስለ ጾታዊ ጥቃቶች እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ግንዛቤ ቢኖራቸውም እነዚህን ድርጊቶች ለማስቀረት ፈቃደኝነት በማህበረሰቡ በኩል አለመኖሩ እና ለዚህ ተግባራት እርምጃ እና ማሻሻያ ለመውሰድ የተዘጋጀውን የህግ እና የፖሊሲ ማእቀፍ አለማወቅ እና በስራ ላይ አለማዋል ከሚጠቀሱት ችግሮች የተወሰኑት ናቸው። እቅድን በጋራ በማውጣት፣ በማስፈጸም እንዲሁም በመገምገም እና በማሻሻል የቅንጅት ስራውን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

በተጨማሪ ጾታዊ ጥቃት በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት መባባስ/አለመባባሱን ለመለየት በሰባት ክልሎች፤ በፌደራል ተቋማትና በአዲስ አበባ ከተማ ክትትል ተካሂዷል። የክትትሉ ግኝቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- ጾታዊ ጥቃትን የተመለከተ ብሔራዊ መርሐ ግብር አለመኖሩ፤ አብዛኞቹ ለአስገድዶ መድፈር ሰለባዎች አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጁ የአንድ መስኮት ማዕከላት በተሟላ አቅም ያለመሥራት፤ የአስተዳደር መዋቅሮች ምንም እንኳን ለጾታዊ ጥቃት ሪፖርቶች አቤቱታ ማቅረቢያ ቦታዎች ቢሆኑም ጾታዊ ጥቃትን የሚመለከት አሠራር/ሰነድ የሌላቸው መሆኑ፤ በሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር እና በዝቅተኛ መዋቅሮች መሀከል ያለው ግንኙነት የላላ መሆን፤ የቅንጅታዊ አሠራር ደካማ መሆን፤ ጾታዊ ጥቃትን ለሚመለከቱ ሥራዎች የበጀት እጥረት መኖር፣ እንዲሁም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በተመለከተ የሚመለከታቸው ክፍሎች በቂ በጀት ያለማግኘታቸው፤ በጾታ፣ በዕድሜ፣ ወዘተ. የተደራጀ መረጃ ያለመኖር እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በየወረዳው እየተሄደ መሥራት ያለመቻል።

**ልጅ ይዘው ለልመና ጎዳና የሚወጡ እናቶች ላይ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ እያስከተለ ያለው ተጽዕኖን በሚመለከት** በኮሚሽኑ የሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት በሀዋሳ ከተማ እና በሲዳማ ክልል በሚገኙ 2 ወረዳዎች (ቦርቻ እና ለኩ ከተማ) 120 ሕፃናትን ጐዳና ይዘው በወጡ 50 እናቶች ላይ የዳሰሳ ጥናት ተሰርቶ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን በጥናቱ ከተካተቱት 98% እናቶች በኢኮኖሚ

ችግር ጎዳና ላይ በመውጣታቸው ምክንያት የልጆቻቸው በህይወት የመኖር፣ የመማር፣ የጤና እና የተሳትፎ መብቶቻቸው እየተጣሰ እንደሆነ፣ እናቶቹም የመስራት፣ የተሳትፎ እና የጤና መብቶቻቸው እየተከበረ አለመሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በቀጣይም በሲዳማ ክልል እና በደቡብ ብሔር፥ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ከሚገኙ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራት የተውጣጡ 14 ሴት እና 16 ወንድ ተሳታፊዎች በተገኙበት የጥናት ግኝቶች ላይ፣ የሴቶችና ህፃናት ቢሮ ነባራዊ ሁኔታ ላይ እንዲሁም በፕላን ኢንተርናሽናል እየተሰሩ የሚገኙ ተግባራትና ተግዳሮቶች ላይ ፅሁፍ ቀርቦ ውይይት የተደረገበት ሲሆን በውይይቱም የችግሩን አሳሳቢነት ተሳታፊዎች ገልፀው ሁሉም ተቋማት እነዚህን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት በኃላፊነት መስራት እንዳለባቸው የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

**ከሴቶች የመስራት መብቶች አኳያ** በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ባህርዳር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት በስድስት ፋብሪካዎች (ኮከብ ቀለም ፋብሪካ፣ ዳሽን ቢራ ፋብሪካ፤ ሞሐ ለስላሳ መጠጦች ፋብሪካ፣ ደስ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ፣ የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ እና ጎንደር ብቅል ፋብሪካ) ላይ የክትትል ስራ ተካሂዷል፡፡ ለፋብሪካዎቹ አስተዳደሮች የሴቶች የሥራ ላይ መብቶችን በተመለከተ ግንዛቤ መስጠት ተችሏል፡፡ ከክትትሉ በኋላ ለፋብሪካዎቹ አስተዳደሮች የሴቶች የሥራ ላይ መብቶችን በተመለከተ ግንዛቤ መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮ ጋር በመተባበር የሴቶችን ለእኩል ስራ የእኩል ክፍያ የማግኘት እና የስራ ላይ ደህንነትና ጤንነት መብት በማስከበር እና በማሟላት ረገድ በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የተመረጡ ተቋማትን አሰራር በመፈተሽ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችን ለይቶ በማውጣት የሚመለከተው አካል ተገቢውን ማሻሻያ እንዲያደርግ የክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡

**በኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው በሚሰሩ ሴቶች ላይ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ያስከተለውን ተጽዕኖ** በተመለከተ በኮሚሽኑ የሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት በስልጤ እና በሀላባ ዞኖች ከሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ፣ ከንግድና ማንፋክቸርንግ መምሪያ እና በተጨማሪም በሁለቱ ዞኖች በኢ-መደበኛ የንግድ ዘርፎች ተሠማርተው ከሚሠሩ በአጠቃላይ ከ30 ሴቶች መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን መረጃው እንደሚያሳየው በኢ-መደበኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ቤተሰብ ማስተዳደር እንዳልቻሉና ለችግር እንደተጋለጡ አንስተው የአሰራር ስርዓት

እንዲዘረጋና የመሸጫ በታዎችና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ለሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ቢሮ በውይይቱ ተገልጿል፡፡

**የህፃናት መብቶችን በተመለከተ**

ኮሚሽኑ በሕግ እንዲሁም በአፈጻጸም የሚታዩ ከህጻናት መብቶች አጠባበቅና አተገባበር ክፍተቶችን ከአለም አቀፍና አህጉራዊ መስፈርቶች አንጻር ለማስጠናት የስራ እቅድ አውጥቶ በስራ ላይ ያሉ ሕጎችንና የተለያዩ ሰነዶችን በመለየት ተጨማሪ ግብአት ለማሰባሰብ አጠቃላይ ውይይትና የተሞክሮ ልውውጥ ከፌደራልና ክልል የፍትህ አካላትና የሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት እንዲሁም ከኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከተውጣጡ 18 ወንድ 8 ሴት ተሳታፊዎች ጋር የምክክር መድረክ ተካሂዷል፡፡

ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም አገራዊ የህፃናት መብቶች ድንጋጌዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ለመገምገም እና ለመከታተል ቀደም ብሎ በዩኒሴፍ ትብብር ተዘጋጅቶ የነበረውን የክትትል ማንዋል መከለስ በማስፈለጉ ኮሚሽኑ የአማካሪ ድርጅት ቀጥሮ ስራውን አስጀምሯል፡፡ ይህ ማንዋልና የመተግበሪያ መሳሪያው ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ስምምነቶችን የአፈጻጸም ደረጃን በቀጣይነት ለመከታተልና አስፈላጊውን ማሻሻያ የሚመለከተው ባለግዴታ አካል በወቅቱ እንዲወስድ ምክረ ሃሣብ ለመስጠት የሚያስችል ነው፡፡

**ኮቪድ-19 በመከላከል የሕፃናት የጤና መብትን ያከበረ የትምህርት ሥርአት እየተተገበረ መሆኑን** ለማረጋገጥ ዋናው መ/ቤት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ጋር በመቀናጀት በጅማ ዞን በተመረጡ 6 ወረዳዎች፤ በአፋር፤ በሱማሌ ክልል በጉርሱም እና ቀብሪበያህ ወረዳዎች በሚገኙ ት/ቤቶች፤ አማራ ክልል የሜጫ እና ደቡብ አቸፈር የወረዳ ከተሞች እና ባህር ዳር ከተማ በሚገኙ አንድ የግልና ሁለት የመንግሥት ት/ቤቶች፤ በአሶሳ ከተማ፣ ሠላም በር፣ ካማሺ ቁጥር 1 እና ካማሺ ቁጥር 2 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፤ እንዲሁም በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በሚገኙ በመስቃን ወረዳና በቡታጅራ ከተማ አራት ት/ቤቶች እና በሲዳማ ክልል ሀዋሳ ከተማ ሁለት ት/ቤቶች እንዲሁም በደቡብ ክልል በወላይታ፣ ጋሞና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአሮሬሳ፣ በቀባዶ እና በበንሳ ወረዳዎች በሚገኙ የትምህርት ቢሮዎችና የሚመለከታቸው የሴክተር ቢሮዎች የተከናወኑ ተግባራት

ላይ ክትትል ተደረጓል፡፡ በክትትሉም ት/ቤቶች በሚከፈቱበት ወቅት የነበረ ንቅናቄ፣ ቅንጅታዊ አሠራርና የአብይና የቴክኒክ ኮሚቴዎች እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ፣ የማስክ አጠቃቀምና የንፅህና መጠበቂያ ማቴሪያሎች አገልግሎት እና ውሃ ያለመኖር፣ በአንዳንድ ት/ቤቶች በአንድ ክፍል ውስጥ ከ50-60 ተማሪዎች እየተማሩ መሆኑ ምልከታ የተደረገ ሲሆን የታዩ ክፍተቶች እንዲታረሙ ግብረ መልስ በቃልና በፅሁፍ ለትምህርት ሴክተር ተቋማት ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ክትትል ለምሳሌ በጉራጌ ዞን በእነሞር ኤነር ወረዳ 11 ት/ቤቶች በመዋቅር ጥያቄ ምክንያት የተዘጉ በመሆኑ የተማሪዎች የመማር መብት መጣሱና በዚህ ወረዳ የሚገኙ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ሃገርአቀፍ ፈተና እንዳልተፈተኑ እንዲሁም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ክልላዊ ፈተና እንዳልተፈተኑ በክትትሉ በመታወቁ ለደቡብ እና ለሲዳማ ክልሎች ለሚመለከታቸው አካላት በሚመለከቷቸው ጉዳዮች ላይ በፅሁፍ ግብረ መልስ የተሰጠ ሲሆን በቡታጅራ ከተማ መድረክ በማዘጋጀት ከደቡብ ክልልና ክትትል ከተደረገባቸው የክልሉ ጉራጌ ዞንና ወረዳዎች ከተውጣጡ የሚመለከታቸው አካላት ባሉበት ውይይት በማድረግ ችግሮች በሚፈቱባቸው አግባብ ላይ የጋራ መግባባት ተደርሷል፡፡

**የአለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ስምምነት አፈፃፀምን በተመለከተ** አራቱ መርሆች (በህይወት የመኖር እና ዕድገት፣ ለህፃናት ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት፣ አድሎ አለማድረግ እና የተሳትፎ መብቶች) መከበራቸውን በደቡብ ክልል በሴክተር መ/ቤቶች፣ በጉራጌ፣ በቤንች ሸኮ፣ በጋሞ ዞኖችና በየም ልዩ ወረዳ ክትትል ተደርጓል፡፡ በክትትሉ የህፃናት መብቶች ስምምነት አስፈፃሚ ኮሚቴ እንቅስቃሴ እና የህፃናት ተሳትፎ የሚገለፅበት መድረክ የህፃናት ፓርላማ እንቅስቃሴ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በክትትሉ በጉራጌ ዞን የህፃናት ፓርላማ እንቅስቃሴን ለማጠናከር በጀት የመመደብ፣ ጽ/ቤት የማመቻቸትና በአዋቂዎች ም/ቤቶች እንዲገኙ በማድረግ በራሳቸው ጉዳይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ መደረጉ ሊበረታታ እና ሊስፋፋ የሚገባው ተግባር መሆኑ ተለይቷል፡፡ ነገር ግን በሌሎች አካባቢዎች በነዚህ ጉዳዮች ላይ ክፍተት መኖሩ፣ ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር የህጻናት መብቶች ኮሚቴ (child rights committee-CRC) አባላት በመመሪያው መሰረት ተገናኝተው ስራዎችን አለመገምገማቸው፣ የመንግስት መዋቅሮች የህፃናትን ጉዳይ የእቅድ አካል አድርገው ስለማከናወናቸው የሚያሳይ የተደራጀ እና የተሟላ መረጃ አለመኖር በክትትሉ ከተለዩት

ክፍተቶች ውስጥ ዋናዎቹ ሲሆኑ አጠቃላይ ግኝቶች እና ምክረ ሃሣቦችን የያዘ ሪፖርት በኢሰመኮ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ተደርጓል።

**በአዲስ አበባ እና በአዳማ የሚገኙ የወጣት ጥፋተኞች የተሃድሶ ማዕከላት** ላይ ክትትል የተካሄደ ሲሆን ወጣት ጥፋተኞችን ለመለወጥ ያለመ የተሃድሶ ሰነድ/መመሪያ የሌለ መሆኑ፣ ለዚህ ጉዳይ ዕቅድ ለመያዝም ሆነ ለመሥራት በጀት የሌለ መሆኑ፣ የሙያ ክህሎት ስልጠናዎች እጥረት፣ የሰብአዊ መብቶች ማስፋፋትን የሚመለከቱ ሥራዎችን የሚመራ አሠራር/ሰነድ አለመኖር እና የአዳማ ማዕከል በበጀት፣ በት/ቤት እና በመምህራን እጥረት የተነሳ መዘጋቱን በክትትሉ ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል። ይህን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመፍትሄ ሃሳቦች ዙሪያ ውይይት የሚደረግ ይሆናል።

**የአካል ጉዳተኞች መብቶችን በተመለከተ**

**አካል ጉዳተኛነትን ማካተት በተመለከተ** እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በመለየት ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ ለማስቻል የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ጠበቆች ማህበር (Ethiopian Lawyers with Disabilities Association - ELDA) ከተባለ ሲቪል ማህበር ጋር የትብብር ስምምነት ተፈርሟል። በዚህ ስምምነት መሰረት በትብብር ሊሰሩ ከታቀዱ ስራዎች ውስጥ ኮሚሽኑ አካል ጉዳተኛነትን ምን ያህል እንደሚያካትትና በአግባቡ ለማካተት ምን ዓይነት እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለበት መለየት፣ ኮሚሽኑ አዲስ የተከራየው የዋና መስሪያ ቤት ሕንፃ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆኑን በመፈተሽ አስፈላጊ ማሻሻያዎች እንዲወሰዱ ማድረግ እንዲሁም ኮሚሽኑ ከ2014 ዓ.ም. ጀምሮ በአዲሱ ስትራቴጂክ ዕቅዱ መሠረት የአካል ጉዳተኛ መብቶች ላይ ስልታዊ በሆነ መልኩ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራባቸው የሚገቡ የመብት ዘርፎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት መለየት መቻል ነው።

**የአካል ጉዳተኞች ፍትህ የማግኘት መብትና ኮቪድ 19** በተመለከተ ኮሚሽኑ ከኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር የዳሰሳ ጥናት አሰርቶ በጥናቱ ግኝቶች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ አካሂዷል። በዳሰሳ ጥናቱ የተለዩት ችግሮችም የፍትህ ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አለመሆን፣ አካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ አገልግሎት

አለመስጠት፣ የመረጃ አሠጣጥና ስርጭት አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ አለመሆን፣ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ የቦታ ለውጥ ሲደረግ መረጃ አስቀድሞ አለመስጠት እና ወረርሽኙን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ አለመሆን ናቸው፡፡ በጥናቱ የተገኙ ችግሮችን ለመፍታትና አካል ጉዳተኞች ፍትሃዊ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑና መብቶቻቸው የተከበሩ እንዲሆኑ ለማስቻል ለሚመለከታቸው አካላት ምክረ-ሃሳቦች ተሰጥቷል፡፡

## ስለ ሰብአዊ መብቶች ማስተማርና ማነቃቃት

**በት/ቤቶች ያሉ የሰብአዊ መብቶች ክበባት ማደራጀትና መደገፍን በተመለከተ** በኢሰመኮ የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት በአማራ ክልል ማዕከላዊ ጎንደር ዞን 6 ት/ቤቶች፣ በደቡብ ጎንደር ዞን 6 ት/ቤቶች፣ አዊ ብሔረሰብ ዞን 14 ት/ቤቶች፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን 7 ት/ቤቶች በአጠቃላይ በ33 ት/ቤቶች ውስጥ ያሉ የሰብአዊ መብቶች ክበባት እንቅስቃሴዎችን መከታተል ተችሏል፡፡ የሰመራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በበኩሉ በዞን 3 በሚገኙ ወረዳዎች አዲስ የሰብአዊ መብቶች ክበባት የሚቋቋምባቸውን 10 ት/ቤቶች የመለየትና ከአሁን በፊት የተቋቋሙትን ክትትል የማድረግ ስራ ሰርቷል፡፡ ለክበባቱ ማጠናከሪያ የሚሆኑ የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች በማዘጋጀት ተሰጥቷል፡፡

**አለም አቀፍ የፀረ-ፆታዊ ጥቃት የ16 ቀናት ዘመቻን** ምክንያት በማድረግ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችና ትንኮሳዎችን በተመለከተ በኮሚሽኑ የተሰራውን የክትትል ውጤትና ምክረ ሃሣብ መነሻ ያደረገና የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆኑ የሕግ ባለሙያዎች ፓናሊስቶች ሆነው የመነሻ ሀሳብ ያቀረቡበት መድረክ የተዘጋጀ ሲሆን ጾታዊ ጥቃትን ለመከላከል የወንዶች አጋርነት አስፈላጊነትን፣ ለመከላከልና ለምላሽ መስጠት ሥራዎች እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን መለየት በማስፈለጉ እንዲሁም የዓመቱ የጸረ-ጾታዊ ጥቃት ዘመቻ መሪ መፈክሮች ላይ አተኩሮ የመሥራት እና የበጀት አስፈላጊነት ላይ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በውይይቱም ከፍትህ አካላት፤ ከሲቪል ማህበራትና ድርጅቶች እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት 25 ወንድ እና 18 ሴት ተሳታፊዎች ተገኝተዋል፡፡ ውይይቱ ከምልክት ቋንቋ ትርጉም ጋር በብሔራዊ ቴሌቪዥን (ኢቢሲ) እንዲተላለፍ በማድረግ ማህበረሰቡና የሚመለከታቸው አካላት ላይ ትኩረት ያደረገ የግንዛቤ እና የውትወታ ተግባር ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪ

የነጭ ሪቫን ቀንን በማስመልከት የኮሚሽኑ ዋና መ/ቤትንና የባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሰራተኞችን ያሳተፈ የፓናል ውይይት በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል።

**አለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀንን** ምክንያት በማድረግ በኢሰመኮ ዋና መ/ቤት የአካል ጉዳተኞች መብት ማክበር ከወረርሽኙ ባሻገር መሄድ እንዳለበት ማስገንዘብን ያለመ ወርክሾፕ ተዘጋጅቶ አካል ጉዳተኞችና ሴቶች ያሉባቸውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ የፍትህ ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ችግሮች፣ እንዲሁም ከወረርሽኙ በኋላ የአካል ጉዳተኞች መብቶች እንዲከበር ምን ማድረግ አለብን በሚሉ ነጥቦች ላይ ውይይት ተደርጓል። በመድረኩ 20 ሲቪል ማህበራት የተሳተፉ ሲሆን የተደረገው ውይይት ተቀርፆ በኢቲቪ በማስተላለፍ በርካታ የማህበረሰብ ክፍል እንዲከታተለው ተደርጓል። በተጨማሪ በጅማ ዞን እና ከጅማ ከተማ የሚመለከታቸው መንግስታዊ ሴክተር ቢሮዎች፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ አካል ጉዳተኞች፣ የእምነት አባቶች፣ አባገዳዎች እና የሲቪክ ድርጅቶችን ጨምሮ 132 ወንድ እና 120 ሴት ተሳታፊዎች በተገኙበት ተከብሯል። ይህ ቀን ሲከበር ስለአካል ጉዳተኝነት፣ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ከሕግ ማዕቀፍ አኳያ እንዲሁም ስለሰብአዊ መብቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የውይይት መነሻ ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ስለተሰሩት ስራዎች እና ስላለው ችግር በሰፊው ውይይት ተካሂዷል። እንዲሁም በኢሰመኮ የሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የአካል ጉዳተኞች ማዕከል ጋር በመተባበር በአካል ጉዳተኞች መብቶች ዙሪያ 250 ባላድርሻ አከላት የተሳተፉበት የምክክር መድረክ ተካሂዷል።

**አለም አቀፍ የህጻናት ቀንን በተመለከተ** በባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካኝነት በወረታ ከተማ በሚገኝ አንደኛ እና መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት ከሚገኙ ተማሪዎችና የት/ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ስለ ሰብአዊ መብቶች ጽንሰ ሃሳብ፣ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፣ ሕገ መንግሥታዊ መብቶችና የአፍሪካ ህፃናት ደህንነት ቻርተርን የሚዳስስ የውይይት መነሻ ጽሁፍ በማቅረብ ውይይት ተደርጎ ተሳታፊዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል።

**አለም አቀፍ የሴቶች ቀንን** ከባህር ዳር ማረሚያ ቤት ጋር በመተባበር "**በተደራጀ የሴቶች ተሳትፎ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እናረጋግጣለን**" በሚል መሪ ቃል ከ61 ወንድ እና

79 ሴት ተሳታፊዎች ጋር የተከበረ ሲሆን የመወያያ ጽሁፍ በማቅረብ እና በራሪ ወረቀቶችን በማሰራጨት ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡

### 2.4 የ2013 በጀት አመት የፋይናንስ አጠቃቀም

ኮሚሽኑ በበጀት አመቱ ሊያከናውን ላቀዳቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ ከመንግስት የተመደበለትን መደበኛ በጀት እና ከተለያዩ አጋር አካላት በፕሮጀክት ድጋፍ መልክ ያገኘውን የፋይናንስ ድጋፍ ተጠቅሟል፡፡ ኮሚሽኑ ለ2013 በጀት አመት ዕቅድ ማስተግበሪያ ከመንግስት መደበኛ በጀት ከተፈቀደለት ብር 95,651,000.00 አመታዊ በጀት ውስጥ በበጀት አመቱ አስራ ሁለት ወራት የተለቀቀው ብር 94,026,332.08 (98.3 በመቶ) ነው፡፡ በዚሁ የበጀት አመት ከተለያዩ የልማት አጋሮች ብር 100,866,353.31 ተገኝቷል፡፡ በጠቅላላው በበጀት አመቱ አስራ ሁለት ወራት ውስጥ ከሁለቱም የፋይናንስ ምንጮች ብር 194,892,655.4 ወደ ኮሚሽኑ ሂሳብ ገብቷል፡፡ ኮሚሽኑ የበጀት ፍላጎቱን ለማሟላት በሚያደረገው ጥረት ከኮሚሽኑ ጋር አብረው የሚሰሩ የልማት አጋር ድርጅቶች ቁጥር በ2012 ዓ.ም. ከነበረው ሶስት ወደ አስር አሳድጓል፡፡

በበጀት አመቱ ከመደበኛ በጀት ከተለቀቀው ብር 94,026,332.08 ውስጥ ብር 92,940,754.87 (ከተለቀቀው በጀት 98.85 በመቶ) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከለጋሽ ድርጅቶች ከተገኘው ብር 100,866,353.31 ውስጥ ብር 48,246,779.38 (ከተለቀቀው በጀት አኳያ 47.83 በመቶ) ስራ ላይ ውሏል፡፡

# 3. የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ጥቅል ግምገማ

## *3.1 ጥንካሬዎች*

በ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ የተስተዋሉ ጥንካሬዎች መካከል የሚከተሉት ዋነኞቹ ናቸው፡፡

- ኮሚሽኑ ያለው የኢንተርኔት ኔትወርክ ፍጥነትና ሽፋን በጣም ዝቅተኛ ቢሆንም ስራን ለማቀላጠፍና፣ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ሰራተኞች ከቤታቸው ሆነው እንዲሰሩ

ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲዲኤምኤ ለተወሰኑ ሰራተኞችና ለአማካሪዎች በመስጠት ስራዎችን ማስቀጠል መቻሉ፤

- በወረርሽኙ ምክንያት የገጽለገጽ ስብሰባዎችንና ስልጠናዎችን በተፈለገው መጠን ማድረግ ባይቻልም ዌቢናሮችንና ሶሻል ሚዲያን ጨምሮ የተለያዩ ሚድያዎችን በመጠቀም የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ የተሻለ ሽፋን እንዲያገኝ መደረጉ፣
- ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጊዜያዊ አስተባባሪዎችን እና ድጋፍ የሚሰጧቸውን አማካሪዎች ከዋናው መ/ቤት በመመደብ ስራዎች በተቀናጀና ተገቢ ፍሰታቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ መደረጉ፤
- ኮሚሽኑ በአጭር ጊዜ የድንገተኛ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ቡድኖች በማቋቋም በሃገሪቱ የሚከሰቱ የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በአፋጣኝ ክትትል እና ምርመራ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካላት ምክረ ሃሣብ ማቅረብ ችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኮሚሽኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን የመከታተል፣ የመሰነድ፣ ሪፖርት የማድረግ እና ምላሽ የመስጠት አቅሙን ለማሳደግ የሚያደርገው ጥረት ጨምሯል፤
- የበጀት ችግርን ለመፍታት ከአጋር አካላት የሚደረጉ ድጋፎች ጨምሯል፤
- የኮሚሽኑን መዋቅር ለማሻሻል በገለልተኛና ብቃት ባለው ተቋም እንዲጠና መደረጉ፤
- የምርጫ ከትትል ስራዎች ማከናወኑ፤

## *3.2 ተግዳራቶች*

ከላይ የተዘረዘሩት ጥንካሬዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዕቅድ አፈጻጸሙ ሂደትም ውስጥ የሚከተሉት ችግሮች በዋናነት ተስተውለዋል፡፡

- መደበኛ በጀት ዘግይቶ በመለቀቁ ምክንያት ለቅ/ጽ/ቤቶች በወቅቱ ባለመድረሱ የታቀዱ ተግባራትን በጊዜው ከመፈፀም አንፃር አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ፤
- ለተከበረው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ የነበረበት በኮሚሽኑ እየተካሄደ ያለውን ተቋማዊ ለውጥ ያገናዘበ ዕቅድ እና ሪፖርት መዘግየት፤

- የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስተባባሪዎች ቢመደቡም የተሟላ የሰው ሃይል ባለመኖር ምክንያት ስራዎችን በሚፈለገው ፍጥነትና ጊዜ ማከናወን አለመቻል፤
- የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እያሳደረ ባለው ተጽዕኖ ምክንያት ሰራተኛው ተረጋግቶ መስራት አለመቻሉ፤
- የኮሚሽኑ የኢንተርኔት አገልግሎት ደካማ መሆን ስራንና ግንኙነትን ቀልጣፋ ማድረግ ባለመቻሉ ዕቅዶችና ሪፖረቶች ወቅታቸውን ጠብቀው አለመድረሳቸው፤
- የኮሚሽኑ መኪኖች የቴክኒክ ችግር ያልባቸው በመሆናቸው የሰብአዊ መብቶች ምርመራዎች እና ክትትሎች በጊዜው እንዲከናወኑ ለማድርግ ተሽከርካሪዎችን በመከራየት ተጨማሪ ወጪ ለማውጣት መገደዱ፤
- የኮሚሽኑ ነፃ ስልክ ጥሪ አገልግሎት ባስፈላጊው ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆኑ እና በከፍተኛ የባለሙያ እጥረትና የሥራ ጫና የተነሳ በተደጋጋሚ መዘጋቱ፤

# 4. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ

## *4.1 የኮሚሽኑ ራዕይ፣ ተልእኮ እና እሴቶች*

**ራዕይ**

ራዕይ - 2030 የሰብአዊ መብቶች ባህል የሰፈነበት (የዳበረባት) ኢትዮጵያ (ሰብአዊ መብቶች ባህል በኢትዮጵያ)

**ተልእኮ**

የሰብአዊ መብቶች ጥበቃን ለሁሉም ማረጋገጥ እና ማራመድ (ማስፋፋት)

**እሴቶች**

| ለእኩልነት፤ ለሰብአዊ ክብር እና ለፍትህ ባለን ቁርጠኝነት መሠረት የኮሚሽኑ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፡ | |
|---|---|
| **ገለልተኝነት** | ኢሰመኮ የመንግስት ተቋም ቢሆንም በገለልተኝነት መርህ የሚሠራ አገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ነው። ነጻና ገለልተኛ አመራርን፤ ባለሙያ የሆኑ ሰራተኞችን እና የፋይናስ አጠቃቀም ነጻነትን በመጠቀም ኮሚሽኑ ከመንግስት አስፈጻሚ አካላት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሌሎች አካላት ያለውን ነጻነትን ያስጠብቃል። |
| **አካታችነት** | የአመራርና የሰራተኛ ጥንቅራችን ብዝሃነት ያለውና አካታች እንዲሆን እንጥራለን። እንዲሁም በተልዕኳችን እና በተግባርና ኃላፊነታችን አድሎንና መገለልን ለማስወገድ እንሰራለን በዚህም የኢትዮጵያን ህዝብ ብዝሃነት እናንጸባርቃለን። |
| **አጋርነትከተጎጂዎች / ለጉዳት ተጋላጭ ከሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር** | የሰብአዊ መብት ጥሰት ከደረሰባቸውና ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ ከሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ጎን በመቆም መብታቸዉን እንዲጠይቁ እና እንዲጠቀሙ እንደግፋለን። ድጋፍ እናደርጋለን። |
| **እውነተኛነትና ሥነ ምግባር** | ሥራዎቻችንን እና የምናቀርባቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች (ምክረሃሳቦቻችን) በእውነታ እና ማስረጃ ላይ እንዲመሠረቱ አስፈላጊውን ጥረት እናደርጋለን፡ ፡ የሙያ ሥነ ምግባሮችን፤ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በከፍተኛ ደረጃ እንጠብቃለን። |

## 5. የዕቅዱ ዓላማ

ኮሚሽኑ ቀልጣፋ፣ ወጭ ቆጣቢና ስኬታማ በሆነ አኳኋን በመፈጸምና የአገልግሎት አስጣጡን በየጊዜው በማሻሻል የተገልጋይ ዕርካታን በተደማሪነት ማሳደግ በሚያስችለው ተቋማዊ አቅም ላይ ለማድረስ በአደረጃጀት፣ አሠራር እና የሠው ኃይል ብቃት ላይ ያተኮሩ መሰረታዊ ተቋማዊ የለውጥ እርምጃዎችን መተግበር የዕቅዱ ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡በመሆኑም የዜጎችን የሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ ማሳደግን፣ በወቅታዊ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዙሪያ የክትትልና ምርመራ ስራዎች ማከናወንን እንዲሁም ለመብቶች ጥሰት ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስን ማዕከል ያደረጉ ክንወኔዎችን መተግበር ዋነኛ ተግባሩ ነው፡፡ እንዲሁም ሰብአዊ መብቶችን የሚጥሱ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ ምርመራ በማድረግ አፋጣኝ መፍትሄዎች እንዲሰጣቸው የሚያስችል ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡

## 6. የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ስትራቴጂያዊ ማዕቀፍ

የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በዋነኛነት ኮሚሽኑ በሕግ የተሰጠውን ተግባር፣ ኃላፊነትና ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችሉና ተቋማዊ ብቃቱን የሚያጎለብቱ አምስት ቁልፍ የውጤት መስኮች/ስትራቴጂክ ግቦች ዕውን ለማድረግ ሰፋፊ የሰብአዊ መብቶችን የማስፋፋትና የማስጠበቅ ስራዎችን በዘጠኝ ፕሮግራሞች ስር በማደራጀት ለመተግበር የተዘጋጀ ነው፡፡ ዘጠኙ ፕሮግራሞች በየሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች አማካይነት ግን ደግሞ ከሌሎች ስራ ክፍሎች ጋር በሰመረ እና በተቀናጀ ብሎም ቁልፍ የውጤት መስኮችን ለማሳካት አስፈላጊ ህብር በሚፈጥሩበት መንገድ ተግባራዊ ይሆናሉ

## 7. ቁልፍ የውጤት መስኮች

### ቁልፍ የውጤት መስክ 1፡ ውጤታማ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት

ባለመብቶችን እና ባለግዴታዎች ስለ ሰብአዊ መብቶች ያላቸውን ዕውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት ማሳደግ፡፡

**ቁልፍ የውጤት መስክ 2 ፡ የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራን ማጎልበት**

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች መከበራቸውን እና ጥሰቶችም ሲከሰቱ በትክክል ምርመራ ተከናውኖ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን እና አጥፊዎችም ተጠያቂ መደረጋቸውን ማረጋገጥ።

**ቁልፍ የውጤት መስክ 3፡ ቁልፍ በሆኑና ቅድሚያ በሚሰጣቸው መስኮች የሰብአዊ መብቶችን ማጎልበት**

- የሴቶችና ህጻናት መብቶች
- የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች
- የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች (ከመኖርያ ቀያቸዉ የተፈናቀሉ ዜጎች) ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች
- የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች
- የኢኮኖሚ፤ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች

ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ በሆኑ የህብረተብ ክፍሎችና ቁልፍ በሆኑ የሲቪል ነጻነትና የኢኮኖሚ ማህበራዊ መብቶች ላይ በማተኮር የሰብአዊ መብቶችን ጥበቃ እና መስፋፋትን ማረጋገጥ።

**ቁልፍ የውጤት መስክ 4፡ ውጤታማ ኮሙኒኬሽን የመረጃ ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) እና አጋርነት**

አውቅናን እንዲሁም ከህብረተሰቡና ቁልፍ ከሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር መስተጋብርን/ ትብብርን በማሳደግ ከፍያለ ውጤት የሚያመጣ የሰብአዊ መብቶች ተግባራትን ማከናወን።

**ቁልፍ የውጤት መስክ 5፡ ተቋማዊ ሪፎርምና መጠናከር**

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ተልዕኮውን፣ ተግባርና ኃላፊነቱን የሚመጥን ገለልተኛ፤ ውጤታማ እና ዘላቂነት ያለው ተቋም እንዲሆን ማስቻል

# 8. የፕሮግራም መስኮች

**የፕሮግራም መስክ 1: የሰብአዊ መብቶች ትምህርት**

**<u>ስትራቴጂዎች</u>**

1.1 ህብረተሰቡ ለጉዳት የተጋለጡ ህብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ጨምሮ ስለ ሰብአዊ መብቶች ያለውን ግንዛቤ እና ትምህርት/ እውቀት ማሳደግ፤

1.2 ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን አቅም እና ቁርጠኝነት መገንባት፤

1.3 የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት መርሃግብሮች ማካተት/ማስረጽ፤

1.3 በሰብአዊ መብቶች ትምህርት ረገድ መተባበርና መደጋገፍ፤

1.5 የሠራተኞች አቅም ግንባታ።

**የፕሮግራም መስክ 2፡ የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ**

**<u>ስትራቴጂዎች</u>**

2.1 ነጻነታቸውን ያጡ ሰዎችን/በጥበቃ ስር ያሉ ሰዎች አያያዝ የሚመለከቱ የሕግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉ ውትወታ/ግፊት ማድረግ፤

2.2 እስር ቤቶች/ማረሚያ ቤቶችና ማቆያ ማዕከላት ላይ ክትትል ማድረግ፤

2.3 በግለሰቦች / በቡድኖች ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ ሰብአዊ መብቶች ጥሰት የሚመለከቱ አቤቱታዎችን በአግባቡ መቀበል፣ መመርመርና መፍትሄ መስጠት፤

2.4 በአሰቸኳይ ጊዜ ወቅት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ መከታተልና መመርመር፤

2.5 የሠራተኛ አቅም ግንባታ።

**የፕሮግራም መስክ 3 ፡ የሴቶችና ህጻናት መብቶች ይስፋፋሉ፣ ይከበራሉ እዲሁም የመብቶች ጥሰቶች ውጤታማ ምላሽ ያገኛሉ፤**

**ስትራቴጂዎች**

3.1 የሴቶችና ህጻናት መብቶችን በተመለከተ ጥናት/ምርመራ ማድረግና የህዝባዊ ምርመራ መድረኮችን ማከናወን ለሁኔታዎችም ውጤታማ ምላሽ እንዲኖር መስራት፤

3.2 በመንግስትና በግል ተቋማት ዘንድ የሴቶችና ህጻናት መብቶች መከበርን መከታተል እና እንዲከበሩ ውትወታ/ ግፊት ማድረግ፤

3.3 የሴቶችና ህጻናት መብቶችን ማራመድ፣ ህዝባዊ ንቅናቄ መፍጠር እና ማብቃት፤

3.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ማለትም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት፣ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች አካላት፣ ከሌሎች አገሮች ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ወዘተ. ጋር ትብብር /መተጋገዝና አጋርነት መፍጠር፤

3.5 የሠራተኞች አቅም ግንባታ።

**ፕሮግራም መስክ 4፡ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች ይስፋፋሉ፣ ይከበራሉ እንዲሁም የመብቶች ጥሰት ውጤታማ በሆነ መልኩ ምላሽ ያገኛሉ፤**

**ስትራቴጂዎች**

4.1 በአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ዙሪያ ጥናት/ምርመራ ማድረግ፤ የህዝባዊ ምርመራ /መጠይቅ መድረክ ማዘጋጀት እና ለጥሰቶች ውጤታማ የመፍተሄ እርምጃዎች እንዲኖር ማራመድ/ማስፋፋት፤

4.2 የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶችን ማራመድ/ማስፋፋት እንዲሁም መብቶችን በተመለከተ ህዝባዊ ንቅናቄ እና አቅም መፍጠር፤

4.3 በመንግስትና በግል ተቋማት ዘንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጡ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች መከበራቸውን ለማረጋገጥ፣ ክትትል ማድረግ እና እንዲከበሩ መወትወት/ግፊት ማድረግ፤

4.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት፥ ማለትም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች አካላት፣ ከሌሎች አገሮች ብሄራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ወዘተ. ጋር መተጋገዝ/ትብብር እና አጋርነት መፍጠር፤

4.5 የሠራተኞች አቅም ግንባታ።

**የፕሮግራም መስክ 5፡ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች የማስፋፋት፣ የማስከበር እና የመብት ጥሰቶች ሲከሰቱ ተገቢውን መፍትሄ ዕንዲያገኙ ማድረግ፤**

**<u>ስትራቴጂዎች</u>**

5.1 የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞችመብቶች ዙሪያ ጥናት/ምርመራ ማድረግ፣ የህዝባዊ ምርመራ መድረኮች ማዘጋጀት እና የመብቶች ጥሰቶች ተገቢው እንዲደረግ ውትወታ/ግፊት ማድረግ እና ማስፋፋት፤

5.2 የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶችን ማስፋፋት፣ ህዝባዊ ንቅናቄ እና አቅም መፍጠር፤

5.3 በመንግስትና በግል ተቋማት የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች አከባበርን በተመለከተ ክትትል እና ውትወታ /ግፊት ማድረግ፤

5.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት፥ ማለትም ከሲቪል ማህበረሰብ፣ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች አካላት፣ ከሌሎች አገሮች ብሄራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ወዘተ. ጋር መተጋገዝ/ትብብር እና አጋርነት መፍጠር፤

5.5 የሠራተኞች አቅም ግንባታ።

**የፕሮግራም መስክ 6: የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ማስፋፋት፣ ማስከበር እና የመብት ጥሰቶች ሲከሰት ተገቢውንመፍትሄ እንዲገኝ ማድረግ**

**<u>ስትራቴጂዎች</u>**

6.1 የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ዙሪያ ጥናት /ምርመራ ማድረግ፣ የህዝብ መጠይቅ መድረኮች ማዘጋጀት እና ለመብት ጥሰቶች ተገቢ መፍትሄ መስጠትን ማስፋፋት/ማራመድ፤

6.2 የሲቪልና ፖለቲካ መብቶችን ማስፋፋት ህዝባዊ ንቅናቄ እና አቅም መፍጠር፤

6.3 የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች መመዘኛዎች በመንግስትና የግል ተቋማት ስለመከበሩ ክትትል ማድረግ እና እንዲከበሩ ግፊት/ ውትወታ ማከናወን፤

6.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት፥ ማለትም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት፣ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች አካላት፣ ከሌሎች አገሮች ብሄራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ወዘተ. ጋር መተጋገዝና አጋርነት መፍጠር፤

6.5 የሠራተኞች አቅም ግንባታ።

**ፕሮግራም መስክ 7፡ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ተማስፋፋት፣ ማስከበር እና የመብት ጥሰቶች ሲከሰቱ ተገቢውን መፍትሄ እንዲያገኑ ማድረግ፤-**

**<u>ስትራቴጂዎች</u>**

7.1 የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ዙሪያ ጥናት /ምርምር/ምርመራ ማድረግ፤ ህዝባዊመጠይቅ መድረኮችን ማዘጋጀት እና ለመብት ጥሰቶች ተገቢ የእርምት/መፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ግፊት/ውትወታ ማድረግ እና ይህንንም ማስፋፋት፤

7.2 የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶችን ማስፋፋት/ማራመድ፣ ህዝባዊ ንቅናቄ እና አቅም መፍጠር፤

7.3 የመንግስትና የግል ተቋማት አሰራር ከኢኮኖሚያ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶችጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ ክትትል ማድረግ እና እንዲሆን ውትወታ/ግፊት ማከናወን፤

7.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት፥ ማለትም የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት፣ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች አካላት፣ ከሌሎች አገሮች ብሄራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ወዘተ. ጋር መተጋገዝና አጋርነት መፍጠር፤

7.5 የሠራተኞች አቅም ግንባታ።

**ፕሮግራም መስክ 8፡ ኮሙኒኬሽን፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) እና አጋርነት (Communications, ICT and Partnership)**

**<u>ስትራቴጂዎች</u>**

8.1 የተቋማዊ እውቅናን በማጎልበት ሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱ መረጃ፣ ሰነዶች እና አገልግሎቶችን ተደራሽነት ማሳደግ፤

8.2 የዕውቀት ሥራ አመራር፤

8.3 በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለመሥራት የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶችንና ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎችን ማዘጋጀት/ማዳበር፤

8.4 ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ (engaging stakeholders)

**የፕሮግራም መስክ 9፡ ተቋማዊ ሪፎርም፣ አቅም ግንባታና ቀጣይነት**

**<u>ስትራቴጂዎች</u>**

9.1 አጠቃላይ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ሥርዓቱን ማሻሻልና ቀልጣፋ የሰው ኃብት ሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋት፤

9.2 የፋይናንስና አስተዳደር ሥርዓቱን በማሻሻልና ግልጽና ዘመናዊ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ቅልጥፍናን ማሳደግ፤

9.3 ቀልጣፋ የሰው ኃብት ልማትና የሠራተኛ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት፤

9.4 ተደራሽና ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር።

## 9. የ2014 ዕቅድ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

ኮሚሽኑ ትኩረት በሚሹ ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ላይ እየሰራ ይገኛል። እነዚህም አካላዊ ደህንነት እና ነጻነቶች፤ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች፤ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች፤ የሴቶች እኩልነት እና ጥበቃ፤ የህጻናት መብቶች፤ የአካል ጉዳተኞች መብቶች፤ የአረጋውያን መብቶች፤ የፍርድ ሂደትን የሚመለከቱ መብቶችን ናቸው። ይህንን ለማረጋገጥ ኮሚሽኑ የሚከተሉትን ዋና ዋና አቅጣጫዎችና ተግባራትን ይከውናል፡-

- በዓመታዊ ዕቅዱ የተቀመጡ ተግባራትን በማከናወንና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ በተቋሙ የተሰማራውን ሰራተኛ በንቃት ባሳተፈ መልኩ ጠንክሮ መስራት
- ሁሉንም የኮሚሽኑ ተግባራት ሥርዓተ-ፆታን ያካተቱ እንዲሁም የሴቶች፣ ሕጻናት እና ሌሎች የመብቶች ጥሰት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ባማከለ አግባብ መፈጸም፣
- ፈጻሚዎች የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅን፣ አያያዝንና አከባበርን ማሻሻል ትኩረት አድርገው የሚፈጽሟቸው ስራዎችን መንግስቱ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችና ጠቃሚ ተመክሮዎች ላይ መመሥረት፣
- ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት፣ ሲቪክ ማሕበራት እና የልማት አጋሮች ጋር ተከታታይ የምክክርና ተግባቦት መድረኮች በማከናወን ተገልጋይ-ተኮር አሰራርን ማጎልበት
- ተቋማዊ የለውጥና ማሻሻያ እንቅስቃሴዎችን ውጤታማነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በኃላፊነትና በቅርብ ክትትልና ድጋፍ መምራት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የሚገኙ ገንቢ ተመክሮዎችን በመቀመር ለየአካባቢዎቹ ነባራዊ ሁኔታ በሚሰማማ መልኩ ማስፋፋት

## 10. በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች እና መፍትሄዎች

***<u>ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች</u>***

- የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፍ ክፍተቶች፤
- ደካማ የሆነ የጸጥታ እና የደህንነት ጥበቃ ሁኔታ፤
- የፖለቲካ ጽንፈኝነት፤

- የተጀመረውን ተቋማዊ የለውጥና መዋቅራዊ አደረጃጀት ማሻሻያ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያጋጥም የአቅም ማነስ፤
- በዕቅዱ የተካተቱትን ተግባራት ለማስፈጸም የሚያስፈልገው በጀትና ባለሙያ የሰው ሃብት በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ላይገኝ መቻሉ፤
- ከአገሪቱ የፖለቲካ ቀውስ የሚመነጩ ሰብአዊ ቀውሶች መበባስ።

***<u>መፍትሄዎች</u>***

- በተለያዩ የስልጠና መርሃ-ግብሮች፣ በእቅድ ዝግጅትና በአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሂደቶች ውስጥ በሚደረጉ ተከታታይ የውይይት መድረኮች ሁሉንም ፈጻሚ ኃይሎች በንቃት በማሳተፍ ስለተቋማዊ ለውጡ ተገቢነትና በለውጥ መሳሪያዎች ዙሪያ ቀጥተኛ የሆነ አመለካከትና አረዳድ እንዲኖር ማድረግ እንዲሁም በለውጡ ግንባታ ቀዳሚ የሆኑትን በማበረታታት ሌሎችንም ፈጻሚዎች ማነሳሳት፤
- ተጨማሪ የመደበኛ በጀት ከመንግስት መጠየቅ፤ አዳዲስ የሃብት (resources) ማሰባሰቢያ ፕሮጀክቶች በመንደፍ ለተለያዩ ድጋፍ-ሰጪ አጋር አካላት በማቅረብ ተጨማሪ ሃብት ለማሰባሰብ ጥረት ማድረግ፤ እና
- ከተለያዩ ምንጮች የሚገኘውን ሃብት ውጤታማ፣ ቆጣቢ፣ ፍትሃዊ እና ግልጽ በሆነ አግባብ ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ።

# 11. የክትትልና ድጋፍ ስርዓት

## *11.1 የዕቅድ አፈጻጸሙ የክትትል ስርዓት*

- ➢ የዕቅዱን አፈፃፀም ሂደት ለመገምገም እንዲቻል የስራ ክፍሎች በየሩብ ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀማቸውን ከሠራተኞቻቸው ጋር ከገመገሙ በኋላ የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ 7 ቀናት ውስጥ ለስትራተጂ ዕቅድ ዝግጅት እና ውጤት አስተዳደር ክፍል ያቀርባሉ፡፡ የስትራተጂ ዕቅድ ዝግጅት እና ውጤት አስተዳደር የስራ ክፍሉም ከየስራ ክፍሎች የመጡ ሪፖርቶችን በማጠናቀር የሩብ ዓመቱ ከተጠናቀቀ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራር

ግምገማ ያቀርባል። የኮሚሽነሮች ጉባዔ ሪፖርቱ በቀረበለት በ5 ቀናት ውስጥ ገምግሞ ማስተካከያ በመስጠት ሪፖርቱን ያፀድቃል። ተስተካክሎ የፀደቀው ሪፖርት የሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ውስጥ ኮሚሽኑ ለሚመለከታቸው ወገኖች ያቀርባል።

- የስትራተጂ ዕቅድ ዝግጅት እና ውጤት አስተዳደር ክፍል በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት በአንድ የሥራ ክፍል የታዩ መልካም ልምዶችን ወደ ሌሎች ክፍሎች ማስተላለፍ እንዲቻል እንዲሁም ሪፖርት የተደረጉ አፈጻጸሞችን በተጨባጭ ለማረጋገጥ በተመረጡ የሥራ ክፍሎች የየሩብ ዓመቱ የመስክ ላይ ክትትል በማድረግ ሪፖርት ያቀርባሉ።

**ተከታታይ ግምገማ ማካሄድ**

- የግምገማ ዋናው ዓላማ አጠቃላይ የዕቅድ አፈጻጸም ለመፈተሽ በመሆኑ፤ በአፈጻጸም የታዩት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይቶ በማውጣት ለሚቀጥለው የትግበራ ሂደት ጠንካራ ጎኑን የበለጠ ለማጠናክርና ድክመቶች በተቻለ መጠን የሚቀረፉበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል የግምግማ ሪፓርት ይዘጋጃል።
- በየደረጃው የሚደረጉት ግምገማዎች የዕቅዱን ቁልፍ ተግባርና አበይት ተግባራት አፈጻጸምን ማዕከል አድርገው የሚከናወኑ ሲሆን፤ በግምገማው ሂደት ውስጥ ነጥረው የሚወጡ የአፈፃፀም ክፍተቶች ዙሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግምገማዊ ሥልጠና በማካሄድ እጥረቶቹ እንዲቀረፉ ይደረጋል።
- ግምገማው በየሥራ ክፍሉ፣ የስራ ክፍሉ ተጠሪ ከሆነበት ኮሚሽነር ጋር እና በኮሚሽነሮች ጉባዔ በአሰራር በተቀመጠ ጊዜ ውስጥ እንዲሁም በተለያዩ የሰብአዊ መብቶች መድረኮች እንደ አመቺነቱ በየጊዜው ይከናወናል።

## *11.2 ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ በጀት*

ለበጀት ዓመቱ ዕቅድ ማስፈፀሚያ ብር 158,616,001.61 ከመደበኛ በጀት የተጠየቀ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 103,030,000 ተፈቅዷል። በተጨማሪም ለበጀት ዓመቱ ዕቅድ ማስተግበሪያ ከተለያዩ የልማት አጋሮች እስከ ብር 241,937,715.24 ለማሰባሰብ ታቅዷል።

## *11.3 የዕቅድ ማስተግበሪያ መርሃ-ግብር*

የእቅድ ማስተግበሪያ መርሃ ግብሩ ከኮሚሽኑ የ2014-2018 ስትራቴጂክ ዕቅድ የተቀዳ ሆኖ ለ2014 በጀት አመት በግብ ስኬት (outcomes)፣ በተግባራት፣ በአመላካች በወሳኝ ምእራፍ (እቅድ) እና በበጀት ምንጭ በሚከተለው የድርጊት መርሃ ግብር እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።የዕቅድ ማስተግበሪያ መርሃ ግብሩ በሀምሌ ወር የፀደቀውን ዝርዝር አመላካችና የሩብ አመት እቅድና በተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተፈቀደለት በጀት መሰረት ተስተካክሎ የቀረበ ነው።

# የ2014 የበጀት አመት የድርጊት መርሃ-ግብር

## ቁልፍ የውጤት መስክ 1፡ ውጤታማ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት

**የፕሮግራም መስክ 1:** <u>የሰብአዊ መብቶች ትምህርት</u>

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| **1** | **ግብ:** ባለመብቶች እና ሲቪል ማህበራት መብታቸውን ለማስከበር የሚያስችላቸው የጎለበተ ዕውቀትና አቅም፤ | | | | | | | | |
| **1.1.1** | **አብይ ተግባር 1፡** በወጣቶች እና ሰብአዊ መብት ዙሪያ ለተመረጡ የወጣት ማህበራት እና አደረጃጀት አባላት እንዲሁም ለሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች 9 የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | | | | | | | | |
| 1.1.1.1 | በስልጠናው ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትን መለየት እና በስልጠናው አተገባበር ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ | በባለድርሻ አካላት ቁጥር | 10+ | | | | | ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች | ውጤታማ የባለድርሻ አካላት ልየታ እና ትብብር |
| 1.1.1.2 | በወጣቶች እና ሰብአዊ መብት ዙሪያ ለተመረጡ 315 ሰልጣኞች የአሰልጣኞች ስልጠናውን መስጠት | በሰልጣኞች ቁጥር | 315 | 105 (3*35) | 105 (3*35) | 105 (3*35) | | ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች | ውጤታማ ስልጠና እና የሰልጣኞች እርካታ |
| 1.1.3 | ከሥልጠና በኋላ ክትትል ማድረግና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት /እንደ አስፈላጊነቱ የማጠናከሪያ ሥልጠና መስጠት | በቅ/ጽ/ቤት ቁጥር | 8 | | | | | ዋና መ/ቤት | ከሥልጠና በኋላ በሰልጣኞች የተከናወኑ ሥራዎች |
| **1.2** | **አብይ ተግባር 3፡** ሁለተኛውን አገር አቀፍ የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች መካከል ማካሄድ | | | | | | | | |
| 1.2.1 | የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር ለማካሄድ የሚረዱ መምሪያዎችን ማሻሻል | በመምሪያ ቁጥር | 3 | | | | | ዋና መ/ቤት | ሶስት የተሻሻሉ መምሪያዎች |
| 1.2.2 | ውድድሩን ለማስጀመር እና ቅንጅት ለመፍጠር የሚያስችል የምክክር መድረክ ማካሄድ | በምክክር መድረክ ቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | የጋራ መግባባት እና ጠንካራ ትብብር |
| 1.2.3 | ክልላዊ የውስጥ ውድድሮችን ማካሄድ | በክልል ውድድር ቁጥር | 12 | | | | | ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች | በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሚደረጉ ውጤታማ የም/ፍ/ቤት ውድድሮች |
| 1.2.4 | የተወዳዳሪዎችን የፅሁፍ መከራከሪያ መመዘን እና የመጨረሻ ዙር አላፊዎችን መለየት | በተወዳዳሪዎች ቁጥር | 48 | | | | | ዋና መ/ቤት | የውድድሩ መጨረሻ ዙር አላፊዎችን መለየት |
| 1.2.5 | አገር አቀፉን የመጨረሻ ዙር ውድድር ማካሄድ | በውድድር ቁጥር | 3 | | | | | ዋና መ/ቤት | ውጤታማ እና አስተማሪ ውድድር |
| **2** | **ግብ :** የጎለበተ የባለግዴታዎች የሰብአዊ መብቶች የማክበር የመጠበቅና የማሟላት አቅምና ቁርጠኝነት | | | | | | | | |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| **2.1** | **አብይ ተግባር 1፡** በፌደራል እና ክልል ደረጃ ለሚገኙ የፖሊስ እና ማረሚያ ቤት አመራሮች እና አባላት በተጠርጣሪዎች እና ታራሚዎች መብት እና አያያዝ ላይ 1 የስልጠና ሰነድ ማዘጋጀትና 10 ስልጠናዎችን መስጠት | | | | | | | | |
| 2.1.1 | የተጠርጣሪዎች እና ታራሚዎች መብቶች እና አያያዝ የማሰልጠኛ ሰነድ ለማሻሻል የሚያስችል የሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ | በዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | የተለዩ የሰልጣኞች የእውቀት እና ክህሎት ክፍተት (የሥልጠና ፍላጎት) |
| 2.1.2 | ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመቀናጀት የማሰልጠኛ ሰነዱን በአዲስ መልክ ማሻሻል | የማሰልጠኛ ሰነድ ቁጥር | 2 | | | | | ዋና መ/ቤት | አንድ የሰልጣኞች የእጅ ማስታዎሻ እና አንድ የአሰልጣኞች መመሪያ |
| 2.1.3 | በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት ለኮሚሽኑ የሥልጠና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | በስልጠና መድረክ ቁጥር | 1 | | | | | | ውጤታማ ስልጠና እና የሰልጣኞች እርካታ |
| 2.1.4 | በተሻሻለው የማሰልጠኛ ማንዋል መሰረት በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ለ350 ሰልጣኞች የአሰልጣኞች ስልጠናዎችን መስጠት | ስልጠና በሚሰጥባቸው ክልሎች ቁጥር | 12 | | | | | ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች | ውጤታማ ስልጠና እና የሰልጣኞች እርካታ |
| 2.1.5 | የሥልጠናውን ውጤታማነት መገምገምና ክትትልን መሠረት ያደረገ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት | በተሰጠ የተክኒክ ድጋፍ ቁጥር | 12 | | | | | ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች | ከሥልጠና በኋላ በሰልጣኞች የሚከናወኑ ሥራዎች |
| **2.2** | **አብይ ተግባር 2፡** ከሴቶች እና ህፃናት የስራ ክፍል ጋር በመተባበር በሴቶች እና ህጻናት መብቶች ዙሪያ ለባለግዴታ አስፈፃሚ አካላት 5 የአሰልጣኞች ስልጠናዎችን መስጠት | | | | | | | | |
| 2.2.1 | በስልጠናው ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትን መለየት እና በስልጠናው አተገባበር ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ | በባለድርሻ አካላት ቁጥር | | | | | | ዋና መ/ቤት | ውጤታማ የባለድርሻ አካላት ልየታ እና ትብብር |
| 2.2.2 | ለተመረጡ 175 ሰልጣኞች ስልጠናውን መስጠት | በሰልጣኞች ቁጥር | 175 | | | | | ዋና መ/ቤት እና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች | ውጤታማ ስልጠና እና የሰልጣኞች እርካታ |
| 2.2.3 | የስልጠና ውጤታማነት መገምገምና ክትትልን መሠረት ያደረገ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት | በስልጠና መድረክ ቁጥር | 5 | | | | | ዋና መ/ቤት እና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች | ከሥልጠና በኋላ በሰልጣኞች የሚከናወኑ ሥራዎች |
| 2.3 | **አብይ ተግባር 3፡** የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞችና ፍልሰተኞች መብቶችን በተመለከተ ለባለግዴታዎች እና ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮችና ስደተኞች መሪዎች ሥልጠና መስጠት (የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች ዲፓርትመንት ጋር በመተባበር) | | | | | | | | |
| 2.3.1 | የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችና ስደተኞችና ፍልሰተኞች መብቶች በተመለከተ የማሰልጠኛ ማኑዋል ማዘጋጀት | የተዘጋጀ ማኑዋል በቁጥር | 1 | | | | | | |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| 2.3.2 | በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት ለኮሚሽኑ የሥልጠና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | በስልጠና መድረክ በቁጥር | 1 | | | | | | |
| 2.3.3 | በተዘጋጀው የማሰልጠኛ ማንዋል መሰረት በ3 ክልሎች ለ105 ሰልጣኞች የአሰልጣኞች ስልጠናዎችን መስጠት | በስልጠና መድረክ በቁጥር | 3 | | | | | | |
| 2.4 | **አብይ ተግባር 4፡** የአካል ጉዳተኞች መብቶችን እና የአረጋውያን መብቶችን በተመለከተ ለባለግዴታዎች ሥልጠና መስጠት (ከአካል ጉዳተኞች መብቶች እና አረጋውያን መብቶች ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር) | | | | | | | | |
| 2.4.1 | የአካል ጉዳጠኞች እና የአረጋውያን መብቶችን በተመለከተ የማሰልጠኛ ማኑዋል ማዘጋጀት | የተዘጋጀ ማኑዋል ቁጥር | 1 | | | | | | |
| 2.4.2 | በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት ለኮሚሽኑ የሥልጠና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | በስልጠና መድረክ ቁጥር | 1 | | | | | | |
| 2.4.3 | በተዘጋጀው የማሰልጠኛ ማንዋል መሰረት በ3 ክልሎች ለ105 ሰልጣኞች የአሰልጣኞች ስልጠናዎችን መስጠት | በስልጠና መድረክ ቁጥር | 3 | | | | | | |
| **2.5** | **አብይ ተግባር 5፡** ሰብአዊ መብቶችን መሰረት ያደረገ አሰራር (HRBA) እና የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDGs) ዙሪያ ለባለግዴታ አስፈፃሚ አካላት(1)፣ ለሚዲያዎች(1) እና ለሙያ ማህበራት(1) ስልጠናዎችን መስጠት | | | | | | | | |
| 2.5.1 | ሰብአዊ መብቶችን መሰረት ያደረገ አሰራር (HRBA) እና የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDGs) አስመልክቶ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ | በፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | የተለዩ የሰልጣኞች የእውቀት እና ክህሎት ክፍተት (የሥልጠና ፍላጎት) |
| 2.5.2 | ሰብአዊ መብቶችን መሰረት ያደረገ አሰራር እና በዘላቂ የልማት ግቦች ዙሪያ የማሰልጠኛ ማንዋል ማዘጋጀት | በማኑዋል ቁጥር | 2 | | | | | ዋና መ/ቤት | አንድ የሰልጣኞች የእጅ ማስታዎሻ እና አንድ የአሰልጣኞች መመሪያ |
| 2.5.2 | በተዘጋጀው የማሰልጠኛ ማኑዋል መሰረት ስልጠናውን በጥናት ለተለዩ 105 ሰልጣኞች መስጠት | በሰልጣኞ ቁጥር | 105 | | | | | ዋና መ/ቤት | ውጤታማ ስልጠና እና የሰልጣኞች እርካታ |
| **3** | **ግብ፡** ያደገ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት መደበኛ በሆኑና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች/ መርሃ ግብሮች/ ሥረዓተ ተምህርቶች መካተት | | | | | | | | |
| **3.1** | **አብይ ተግባር 1፡** በመጀመሪያ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሙያ ሥልጠናዎች፣ በሕግ አስከባሪዎችና የደህንነት ኃላፊዎች ሥልጠናዎች፣ በማህበራዊ አገልግሎት አቅራቢዎች ሥልጠና የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን ማካተት | | | | | | | | |
| 3.1.1 | የሰብአዊ መብቶችን በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ማሰልጠኛ ተቋማት | በመምሪያቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | ጥራት ያለው የአካቶ መምሪያ |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | ትምህርትና ሥልጠና ለማካተተት የሚያስችል መምሪያ ማዘጋጀት | | | | | | | | |
| 3.1.2 | በተዘጋጀው መምሪያ መሰረት ለኮሚሽኑ የስልጠና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት | በሰልጣኞች ቁጥር | 24 | | | | | ዋና መ/ቤት | ውጤታማ ስልጠና እና የሰልጣኞች እርካታ |
| 3.1.3 | በሚመለከታቸው ተቋማት አማካኝነት የካሪኩለም ግምገማ እንዲደረግ ግፊ ማድረግ እና ለሚደረገው ግምገማ ቴክኒካዊ እገዛ መስጠት | በተቋማት ቁጥር | 5+ | | | | | ዋና መ/ቤት | ውጤታማ ቴክኒካዊ ድጋፍ እና የካሪኩለም ግምገማ |
| 3.1.4 | የካሪኩለም ግምገማ ግኝቶች እና የሰብአዊ መብቶች ትምህርት ተካቶ ተግባራትን በተመለከተ 2 አውደ ጥናቶችን ማካሄድ | በአውደ ጥናት ቁጥር | 2 | | | | | ዋና መ/ቤት | የጋራ መግባባት እና ትብብር |
| 3.1.5 | የሰብአዊ መብቶች ትምህርት በካሪኩለም መካተቱን ለማረጋገጥ የሰብአዊ መብት ዘዴዎችን ሥልጠናን ጨምሮ ማማከርና መደገፍ | በምክርና ድጋፍ ቁጥር | 5+ | | | | | ዋና መ/ቤት | ውጤታማ ስልጠና፣ የሰልጣኞች እርካታ እና ድጋፍ |
| **3.2** | **አብይ ተግባር 2፡** የሰብአዊ መብቶች ትምህርት የዘላቂ ልማት ግቦች(4.7) ተግባራዊነትን መከታተል እና በሰብአዊ መብቶች ትምህርት የዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የሰጡት ምክረ ሃሳብ መተግበሩን ማረጋገጥ | | | | | | | | |
| 3.2.1 | የዘላቂ ልማት ግብ 4.7 እና በግቡ ላይ የተሰጡ ምክረ ሃሳቦችን አስመልክቶ የማብራሪያ ፅሁፍ ማዘጋጀት እና በ2 መድረኮች ለባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅ | በሁነቶች ቁጥር | 2 | | | | | ዋና መ/ቤት | የጋራ መግባባት እና ትብብር |
| 3.2.2 | የኢትዮጵያ አገራዊ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት አገር አቀፍ ኮሚቴ እንዲቋቋም እና እቅድ/የድርጊት መርሃግብር እንዲዘጋጅ መወትወት | በተዘጋጀ መርሀ ግብር ቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | የጋራ መግባባት እና ትብብር |
| 3.2.3 | የዘላቂ ልማት ግብ 4.7 ምክረ-ሃሳቦችን በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ማድረግ | በክትትል ቁጥር | 12 | | | | | ዋና መ/ቤት | የውትወታ፣ ድጋፍ እና እገዛ መስኮችን መለየት |
| 3.2.4 | አገር አቀፍ ኮሚቴ እንዲቋቋም የሚያስችል አገር አቀፍ መድረክ ማዘጋጀት | በተሳታፊ ቁጥር | 60 | | | | | ዋና መ/ቤት | የአገር አቀፍ ኮሚቴ ምስረታ |
| 3.2.5 | ከትምህርት ሚ/ር፣ክልላዊና የወረዳ ትምህርት ቢሮዎች ጋር እንዲሁም ከዩንቨርስቲዎች፣ የሥልጠና ተቋማት፣ የፍትህ ሴክተር፣ የሰብአዊ መብቶች | በክትትል ቁጥር | 40 | | | | | ዋና መ/ቤት | *የጋራ መግባባት እና ትብብር<br>*የውትወታ፣ ድጋፍ እና እገዛ |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | ትምህርት የድርጊት መርሃ ግብር ኮሚቴ ጋር በመሆን በዘላቂ ልማት ግብ 4.7 በተመለከተ የምክክር መድረኮችን በማመቻቸት የአገራዊ እቅዱን አፈጻጸም ደረጃን መከታተል | | | | | | | | መስኮችን መለየት |
| 3.2.6 | በዘላቂ ልማት ግብ 4.7 ላይ ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣ | በሪፖርት ቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | የአገራዊ አፈፃፀም ደረጃን ማወቅ |
| **4** | **ግብ፡** የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን ለማካተትና ለማስፋፋት ያደገ የቁልፍ ባለድርሻ አካላት መተጋገዝና ትብብር፤ | | | | | | | | |
| **4.1** | **አብይ ተግባር 1፡** በሰብአዊ መብቶች ትምህርት አግባብነት ካላቸው አገር አቀፍ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መተባበር | | | | | | | | |
| 4.1.1 | አገር አቀፍ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት ማፒንግ ማዘጋጀት | በማፒንግ ቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን መለየት |
| 4.1.2 | የድርጊት መርሃ ግብር አፈጻጸሙን በየወቅቱ ውይይት በማድረግ መገምገም | በግምገማ መድረክ ቁጥር | 1 | | | | | ዋና መ/ቤት | *የውትወታ፣ ድጋፍ እና እገዛ መስኮችን መለየት |
| **5** | **ግብ፡** ያደገ የሠራተኞች የሰብአዊ መብቶች ትምህርት ፕሮግራሞችን የመቅረጽ፣ የመተግበር፣ አፈጻጸምን የመከታተልና የመገምገም አቅም፤ | | | | | | | | |
| **5.1** | **አብይ ተግባር 1፡** የሰራተኞችን ሙያዊ እና የመፈፀም አቅም መገንባት | | | | | | | | |
| 5.1.1 | ሰብአዊ መብቶችን መሰረት ያደረገ አሰራር (HRBA) እና የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDGs) አስመልክቶ የአሰልጣኞች ስልጠና ለኮሚሽኑ ሥልጠና ባለሙያዎች መስጠት | በሰልጣኞች ቁጥር | 24 | | | | | ዋና መ/ቤት | የሰልጣኞች እርካታ እና የጎለበተ የሰራተኞች አቅም |
| 5.1.2 | ሰብአዊ መብቶችን መሰረት ያደረገ አሰራር (HRBA) እና የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDGs) አስመልክቶ ለኮሚሽኑ ሰራተኞች ሥልጠና መስጠት | በሰልጣኞች ቁጥር | 70 | | | | | ዋና መ/ቤት | የሰልጣኞች እርካታ እና የጎለበተ የሰራተኞች አቅም |
| 5.1.3 | ለኮሚሽኑ የስልጠና ባለሙያዎች የሰብአዊ መብቶች ትምህርት የሥልጠና አሰጣጣጥ ዘዴ ስልጠና መስጠት | በሰልጣኞች ቁጥር | 24 | | | | | ዋና መ/ቤት | የሰልጣኞች እርካታ እና የጎለበተ የሰራተኞች አቅም |
| 5.1.4 | የክፍሉን ስራ የሚመራ ስትራቴጂ፣ የአሰራር መመሪያ፣ ዘዴዎች፣ ቼክሊስቶች ማዘጋጀት | *የተዘጋጁ ሠነዶች ብዛት<br>*የተከለሱ ሠነዶች ብዛት | *5 ሠነዶችን ማዘጋጀት<br>*5 ሠነዶችን መከለስ | | | | | ዋና መ/ቤት | *5 ሠነዶች ተዘጋጅተዋል<br>*5 ሠነዶች ተከልሰዋል |
| | ጠቅላላ | የመንግስት ጠቅላላ በጀት ድምር- ብር፤ 1,523,394<br>የፕሮጀክት ጠቅላላ በጀት ድምር- ብር፤ 29,567,296<br>የሁለቱም ድምር- ብር፤ 31,090,690 | | | | | | | |

**የፕሮግራም መስክ 2፡ የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ**

**የሥራ ክፍል፡** <u>የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ</u>

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | **አበይት ተግባራት** | | | | | | | | |
| | **አብይ ተግባር 1፡** ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ መኖሩን ማረጋገጥ | | | | | | | | |
| 1.1 | በፌደራል ደረጃ የእስረኞች አያያዝን የሚመለከቱ ዝርዝር ደንቦች እና መመሪያዎች ላይ ጥናት ማድረግ እና የክልል የማረሚያ ቤቶችን አዋጅ ለመከለስ የሚያግዝ ሞዴል ሕግ ማዘጋጀት | የተከናወነ ጥናት ውጤት እና የተዘጋጀ ሞዴል ሕግ | 3 ደንቦች/ መመሪዎች እና 1 ሞዴል ሕግ | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | የተሻሻሉ መመሪያዎች እና ደንቦች የተሻሻሉ የክልል ማረሚያ ቤቶች አዋጆች |
| 1.2 | በ 1.1. ላይ በሚደረጉት ጥናቶች መሰረት የውይይት እና የውትወታ መድረኮችን ማዘጋጀት | የተካሄዱ የምክክር አውደ ጥናቶች ብዛት | 3 የምክክር መድረኮች | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | የተሻሻሉ መመሪያዎች እና ደንቦች፤ የተሻሻሉ የክልል ማረሚያ ቤቶች አዋጆች |
| 1.3 | በፌደራል እና በክልሎች የፖሊስ የእስረኛ ማቆያ ቦታዎችን በተመለከተ ያሉ ሕጎችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎች ላይ ጥናት ማድረግ እና የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት | የተከናወነ ጥናት ውጤትና ተግባራዊ የሆኑ ምክረ ሃሳቦች | የጥናት ውጤት ሪፖርት እና 3 የምክክር መድረኮች | | | | | ዋናው መስሪያቤት እና 3 ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | የተሻሻሉ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች |
| | **አብይ ተግባር 2፡** በሕግ ጥላ ስር ላሉ ሰዎች የተሻሻለ አያያዝና ጥበቃና ክትትል ማድረግ | | | | | | | | |
| 2.1 | የክትትል መመሪያዎችን፣ ቼክሊስቶችን እና የአሰራር ዘዴዎችን መከለስ፣ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ማከናወን | የተከለሱ መመሪያዎችና የአሰራር ዘዴዎች | 1 የተሻሻለ መመሪያ፣ 1 ጥራዝ ቼክሊስት፣ 2 አቅም ግንባታ ስልጠናዎች | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት | የተተገበረ የክትትል መመሪያ እና ቼክሊስቶች |
| 2.2 | በፌደራል እና በክልል ማረሚያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች እና ማቆያዎች ድንገተኛ እና መደበኛ ክትትል ማድረግ (የሴቶች እና ህፃናት እስረኞችን ጉዳይ ጨምሮ) | የተከናወነ ክትትል | በ 20 ማረሚያ ቤቶች እና እስር ቤቶች ላይ ክትትል ጉብኝቶች ማድረግ | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | የተተገበሩ ምክረ ሀሳቦች |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| 2.3 | ሀገራዊ የማረሚያ ቤቶች የሰብአዊ መብቶች አያያዞች አመታዊ ሪፖርት ማውጣት እና ሰብአዊ መብቶች የላቀ አያያዝ ደረጃዎች አወጣጥ ስነስርአት መመሪያ ማዘጋጀት፣ | አመታዊ ሪፖርት እና የደረጃ አወጣጥ ስነስርአት መመሪያ | ደረጃዎችን የያዘ አንድ አመታዊ ሪፖርት | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት (ከቅርንጫፍ ፅ/ቤት በሚገኙ ግብአቶች) | የሰብአዊ መብቶች የላቀ አያያዝ ደረጃዎችን የያዘ አመታዊ ሪፖርት |
| 2.4 | ሰብአዊ መብቶች የላቀ አያያዝ ደረጃዎች ይፋ ማድረጊያ ፕሮግራም ማዘጋጀት | ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት ፕሮግራም | 1 ሀገራዊ ደረጃዎችን ይፋ የማድረጊያ ፕሮግራም | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት | የተሳካ፣ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት ሪፖርት የማውጣት እና ደረጃ ይፋ የማድረጊያ ፕሮግራም |
| | **አብይ ተግባር 3፡** የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ምርመራና ክትትል ማድረግ | | | | | | | | |
| 3.1 | የሰብአዊ መብት ጥሰት አቤቱታ አቀራረብ ስነስርአት መመሪያን መከለስ፣ አቅም ግንባታ ተግባራትን ማከናወን (የህፃናት፣ ስነፆታና አካልጉዳተኝነት አካታችነትን ጨምሮ) | የተከለሱ መመሪያዎችና የአሰራር ዘዴዎች | 1 የተሻሻለ መመሪያ፣ 3 አቅም ግንባታ ስልጠናዎች | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት (ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሚሳተፉበት) | የተተገበረ መመሪያ |
| 3.2 | የሰብአዊ መብት ጥሰት አቤቱታአቀራረብ እና ስነስርአት መመሪያን አትሞ ማሰራጨት እና የግንዛቤ እና የማስተዋወቅ ተግባራትን ማከናወን | የመመሪያው መታተም ፣ መሰራጨጥ እና መተዋወቅ | 1 ተሸሻለ መመሪያ፣ 5 የኮሙኒኬሽን ማቴሪያሎች | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | በህብረተሰቡ እና ባለድርሻ አካላት ዘንድ የሚታወቅ ሰብአዊ መብት ቅሬታ አቀራረብ እና ስነስርአት መመሪያ |
| 3.2 | የሰብአዊ መብት ጥሰትን በሚመለከት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መቀበል፣ በራስ ተነሳሽነት መመርመር (ማማከር፣ ማስማማት፣ ጉዳዩን ወደ ሌላ አካል መምራት እና ጉዳዩን መመርመር) | ምላሽ የተሰጠባቸው ቅሬታዎች ብዛት እና የቅሬታ አቅራቢዎች እርካታ መጠን | ከቀረቡ ቅሬታዎች ውስጥ ለ 98 በመቶ ምላሽ መስጠት እና 90 በመቶ እርካታ መጠን | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | ዒላማውን በማሳካት ተገቢ ምላሽ የተሰጠባቸው አቤቱታዎች እና ተከናወኑ ምርመራዎች |
| 3.3 | አውቶሜትድ የሆትላየን ስርአት መተግበር | የተተገበረ የሆትላየን ስርአት | የሆትላየን ስርአት መተግበር | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት | በሆትላየን በመጠቀም አቤቱታዎችን እና ጥቆማዎችን መቀበል |
| 3.4 | ጥናት በማድረግ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ውጤታማ የጉዳይ አመራር (ሪፈራል) ሥርዓት መዘርጋት | የተዘረጋ የጉዳይ አመራር (ሪፈራል) ሥርዓት | መመራት ካለባቸው ጉዳዮች 98 በመቶ በውጤታማነት መምራት | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና 4 ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | ወደሚመለከታቸው አካላት ተመርተው የተፈቱ ቅሬታዎች ብዛት |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| 3.5 | በፎረሞች ላይ መሳተፍ፣ ከአካባቢ ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ የኬዝ አስተባባሪዎች ውይይት ማድረግ | ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚፈጠር ግንኙነት | 1 የኬዝ አስተባባሪዎች ውይይት | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት (ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሚሳተፉበት) | በባለድርሻ አካላት ጋር የቅርብ ግንኙነት መፍጠር፣ የተጠናከረ የተቋሙ ኬዝ አስተባባሪዎች ግንኙነት |
| | **አብይ ተግባር 4፡** የአደጋ ጊዜ የሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ክትትል እና ምርመራ ማድረግ | | | | | | | | |
| 4.1 | የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርአቶች ላይ ክትትል ማድረግ | በቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርአቶች ላይ የተደረገ ክትትል | በፌደራል እና በ 4 ክልሎች የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርአቶች ላይ ከሰብአዊ መብቶች አንፃር ክትትል ማድረግ | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና 4 ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | የክትትል ሪፖርት እና ምክረ ሀሳቦች |
| 4.2 | የቅድመ ማስጠንቀቂያ የአውቶሜትድ ስርአት መዘርጋት እና በሲስተሙ ላይ የኮሚሽኑን አቅም መገንባት | የተዘረጋ ስርአት እና የተዘጋጁ የሥልጠና ፕሮግራሞች ብዛት | 1 አውቶሜትድ ሲስተም እና 4 አቅም ግንባታ ስልጠናዎች | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት (ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሚሳተፉበት) | ተግባራዊ የሆነ የኮሚሽኑ አውቶሜትድ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርአት ተግባራዊ |
| 4.3 | ክስተተቶችን መሠረት ያደረገ የአደጋ ወቅት የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ክትትል ማድረግና የክትትል ግኝቶችንና ምክረ ሃሳቦችን ማውጣት | ምርመራ የተደረገባቸው የአደጋ ክስተቶች ብዛት | ከተከሰቱ ክስተቶች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት ላይ ክትትል ማድረግ | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | የቀረቡ ሪፖርቶችና የተተገበሩ ምክረ ሃሳቦች ብዛት |
| 4.4 | በግኝቶች እና በምክረ ሀሳቦቹ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያያት የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣ የአፈፃፀም ክትትል ማድረግ | የተዘጋጁ ምክክር መድረኮች | 80 በመቶ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ መሆን | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | በዒላማው መሰረት የተተገበሩ ምክረ ሀሳቦች |
| 4.5 | ከባለድርሻ አካላት ጋር የግንኙነት መስመር መፍጠር፣ ለመረጃ ምንጮች አቅም ግንባታ ተግባራት ማከናወን | የተከናወኑዪአቅም ግንባታ ተግባራት | በሁሉም ክልሎች ተፈጠረ ግንኙነት | | | | | ዋናው መስሪያ ቤት እና ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች | የተሳለተ መረጃ ፍሰት እና የምክረ ሀሳቦች መተግበር |
| | የክፍሉን ስራ የሚመራ ስትራቴጂ፣ የአሰራር | *የተዘጋጁ ሠነዶች | *5 ሠነዶችን | | | | | ዋና መ/ቤት | *5 ሠነዶች ተዘጋጅተዋል |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | መመሪያ፣ ዘዴዎች፣ ቼክሊስቶች ማዘጋጀት | ብዛት<br>*የተከለሱ ሠነዶች ብዛት | ማዘጋጀት<br>*5 ሠነዶችን መከለስ | | | | | | *5 ሠነዶች ተከልሰዋል |
| | ጠቅላላ | የመንግስት ጠቅላላ በጀት ድምር ብር፤ 1,717,277<br>የፕሮጀክት ጠቅላላ በጀት ድምር ብር፤ 12,972,403<br>የሁለቱም ድምር ብር ፤ 14,689,680 | | | | | | | |

## ቁልፍ የውጤት መስክ 3፡ ቁልፍ በሆኑና ቅድሚያ በሚሰጣቸው መስኮች ሰብአዊ መብቶችን አያያዝ ማጎልበት

**የፕሮግራም መስክ 3 ፡** <u>የሴቶች እና ህጻናት መብቶች አፈፃፀም ይጠናከራል እንዲሁም የመብቶች ጥሰቶች አጥጋቢ መፍትሔ ያገኛሉ፤</u>

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| **3.1** | **አብይ ተግባር 1፡** የሕግ ማዕቀፍ እና አፈጻጸሙ ከሕገ መንግስቱ፣ ከአህጉራዊ እና ዓለም ቀፋዊ ስምምነቶች እና መስፈርቶች ጋር እንዲጣጣም ማስቻል | | | | | | | | |
| 3.1.1 | በተለይ ከሴቶች ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች አንጻር ብሄራዊ ሕጎች ከአለም አቀፍ የጾታ እኩልነት እና የሴቶች መብቶች አንጻር የዳሰሳ ጥናት ማድረግ | ሕጉና አተገባበሩ ላይ ክፍተቶችን የሚያሳይ የጥናት ሪፖርት | 1 የጥናት ውጤት | | | | | ዋና መ/ቤት | |
| 3.1.2 | የውትወታ እና የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | * የወርክሾፕ ብዛት<br>* የተሳታፊዎች ብዛት | * 1 ወ/ሾፕ<br>* 50 ተሳታፊዎች | | | | | | |
| 3.1.3 | የጥናቱን ውጤት ማስተዋወቅ እና በስፋት ማሰራጨት (ድረገጽ መጠቀም፣ ረፖርቶች፣ መግለጫዎች ማዘጋጀትና እንዲዘገቡ ማድረግ) | የሚድያ ሽፋን | የተሻለ የሚድያ ሽፋን | | | | | | |
| 3.1.4 | የህጻናት መብቶች ላይ በተለይም አለም አቀፍና አህጉራዊ ህጎች በአገራዊ የሕግና ፍትህ ስርአት ውስጥ መካተታቸውን የሚያሳይ የሕግ ጥናት ማካሄድ | | | | | | | ዋና መ/ቤት | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| 3.1.5 | የውትወታ፣ ምክክር ወርክሾፖችን ማዘጋጀት | * የወርክሾፕ ብዛት<br>*የተሳታፊዎች ብዛት | * 1 ወ/ሾፕ<br>* 50 ተሳታፊዎች | | | | | ዋና መ/ቤት ከቅ ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | |
| 3.1.6 | የጥናቱን ውጤት ማስተዋወቅ እና በስፋት ማሰራጨት (ድረገጽ መጠቀም፤ ረፖርቶች፣ መግለጫዎች ማዘጋጀትና እንዲዘገቡ ማድረግ) | * የተላለፉ መልእክቶች ብዛት<br>* የሚዲያ ሽፋን | * 3 መልእክቶች<br>* የተሻለ የሚዲያ ሽፋን | | | | | ዋና መ/ቤት | |
| 3.1.7 | በአፋር፣ ሶማሌና ሲዳማ ክልሎች የቤተሰብ ሕግ የማዉጣት ሂደት እንዲነቃቃና ሰብአዊ መብቶችን ያማከለ እንዲሆን ድጋፍና ውትወታ ማድረግ | *የተዘጋጀ የውትወታ እቅድ<br>*የምክክር መድረክ ብዛት<br>*የመንግስት አካላት የቁርጠኝነት ደረጃ | * 3 የውትወታ እቅዶች<br>* 3 የምክክር መድረኮች<br>* የተሻለ የመንግስት አካላት የቁርጠኝነት | | | | | ዋና መ/ቤት፣ ሰመራ፣ጅግጅጋና ሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች | |
| 3.1.8 | የመንግስት አካላት የህጻናት እና ሴቶችን መብቶች በማክበርና በመጠበቅ ረገድ ያለባቸውን ግዴታ የሚያሰይ የውሳኔ ሀሳብ/የፖሊሲ መግለጫ/ማብራሪያ ማዘጋጀት | ይፋዊ መግለጫዎች/ ማብራሪያይዘትና ብዛት | 4 መግለጫዎች/ ማብራሪያ | | | | | ዋና መ/ቤት ከቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | |
| 3.1.9 | የህጻናት እና ሴቶችን መብቶች በተመለከተ በፌደራልና ክልላዊ የሕግ ማውጣት ሂደቶች ላይ የምክር አገልግሎቶችን መስጠት | የምክር አገልግሎቶች ቁጥር | 3 የምክር አገልግሎቶች | | | | | ዋናመ/ቤት ከሰመራ፣ ጅግጅጋ እና ሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | |
| **3.2** | **አብይ ተግባር 2**፡ ባለግዴታዎች የህጻናት እና የሴቶች መብቶችን እንዲያከብሩ እና እንዲ ያስጠብቁ የተሻለ ግንዛቤ ማስጨበጥ | | | | | | | | |
| 3.2.1 | በፌደራልና በክልል ደረጃ ለሚገኙ ሕግ አውጪዎች የጾታ እኩልነት፣ የሴቶች እና የህጻናት መብቶችን የሚመለከቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት | * የተሳታፊዎች ብዛት<br>* የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ብዛት | * 180 ተሳታፊዎች(30% ሴቶች)<br>* 9 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች | | | | | ዋና መ/ቤትና ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች | |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| 3.2.2 | በሕገ ወጥ የሴቶች እና ዝውውር፣ የጉልበትና የወሲብ ብዘበዛና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ለሚመለከታቸው ባለግዴታዎች የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | * በምክክር መድረኮች የተሳተፉ ባለግዴታዎች ቁጥር<br>* የምክክር መድረኮች ብዛት | * 225 ባለግዴታዎች ጋር ምክክር መካሄድ<br>* 9 የምክክር መድረኮች | | | | | ዋና መ/ቤትና ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች | |
| 3.2.3 | ለሚዲያ ባለሙያዎች የሴቶችና ህጻናት መብቶች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት * በሪፖርት አቀራረብና ፕሮግራሞች ላይ የተደረጉ ለውጦች መኖራቸውን መከታተል | * የስልጠና ተሳታፊዎች ብዛት<br>* የሚዲያ ሽፋን ደረጃ | * 50 ተሳታፊዎች (30% ሴቶች)<br>* የሚዲያ ሽፋን መጨመር | | | | | ዋና መ/ቤት ከቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | |
| 3.2.4 | የሴትልጅ ግርዛትን እና የህጻናት መዳርን እ.አ.አ. በ2025 ለማስቀረት መንግስት ያስቀመጠውን ግብ አፈጻጸም ከሰብአዊ መብቶችና ከዘላቂ የልማት ግቦች አንጻር ለመመርመር የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | የዳሰሳ ጥናት መካሄድ | 1 የውሳኔ ሃሳብ የያዘ የዳሰሳ ጥናት | | | | | | |
| 3.2.5 | የጥናቱ ውጤት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረግ | *የውይይት ተሳታፊዎች ብዛት<br>*የውሳኔ ሃሳቦችን ለመተግበር ቁርጠኝነት | 180 ተሳታፊዎች<br>*መሻሻል ይደረግባቸዋል በሚል ቃል የተገባባቸው የውሳኔ ሀሳቦች | | | | | | |
| 3.2.6 | የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎን በተመለከተ ብሄራዊ ወርክሾፕ ማዘጋጀት | *የተዘጋጁ ወርክሾፖች ብዛት;<br>*የተሳታፊዎች ብዛት;<br>* የሚዲያ ሽፋን ደረጃ | * 2 ወርክሾፖች<br>* 60 ተሳታፊዎች<br>*የተሸለ የሚዲያ ሽፋን | | | | | | |
| **3.3** | **አብይ ተግባር 3፡** ሴቶች እና ህጻናት መብታቸውን መጠየቅ እንዲችሉ ማብቃት | | | | | | | | |
| 3.3.1 | የሴትልጅ ግርዛትን እና የህጻናት መዳርን በተመለከተ የማህበረሰብ ውይይቶችን ማካሄድ | *የማህበረሰብ ውይይቶች ብዛት<br>*የተሳታፊዎች ብዛት | * 16 የማህበረሰብ ውይይቶች<br>* 240 ተሳታፊዎች | | | | | በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች | |
| 3.3.2 | አመታዊ የሴቶች እና ህጻናት ቀናትን በተለያዩ ተግባራት ማክበር (ፓናል | *የተላለፉ መልእክቶች ብዛት | * 1 ግልጽ መልእክት መተላለፍ | | | | | ዋና መ/ቤትና ሁሉም ቅርንጫፍ | |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | ውይይቶች ወዘተ.) | *የተዘጋጁና የተሰራጩ የመረጃና ተግባቦት ሰነዶች ብዛት<br>*የፓናል ውይይቶች ብዛት | *1 የመረጃና ተግባቦት ሰነድ ዝግጅት<br>*9 የፓናል ውይይቶች | | | | | ጽ/ቤቶች | |
| 3.3.3 | የህጻናት ክበባትን፣ የህጻናት ፓርላማዎችን ለመደገፍና ለማነቃነቅ የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | *ድጋፍ ያገኙ ክለቦች/ፓርላማዎች ብዛት<br>*የምክክር መድረኮች ብዛት | * 10 ህጻናት መር ክለቦች/ፓርላመንቶችን<br>* 2 የምክክር መድረኮች | | | | | ዋና መ/ቤትና ሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች | |
| 3.3.4 | ለ ህጻናት ፓርላማ አባላት እና የሲቪል ማህበረሰብ አባላት በህጻናት መብትና ጾታ እኩልነት ላይ የ5 ቀን የአስልጣኞች ስልጠና መስጠት (ከሰብአዊ መብት ትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር) | *የኣሰልጣኞች ስልጠና የወሰዱ ብዛት<br>* የሲቪል ማህበረሰብ አባላት ሰልጣኞች ቁጥር በጾታ | * 50 የኣሰልጣኞች ስልጠና የወሰዱ<br>* 25 የሲቪል ማህበረሰብ አባላት ሰልጣኞች (30% ሴቶች) | | | | | ዋና መ/ቤት ከቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | |
| **3.4** | **አብይ ተግባር 4፡** የበለግዴታዎች የህጻናትን እና የሴቶችን መብቶች አተገባበር የተሻለ እንዲሆን ማስቻል | | | | | | | | |
| 3.4.1 | በኢንዱስትሪ ፓርኮች እና በማረሚያ ቤቶች በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተመለከተ ክትትል ማድረግ<br>* የውሳኔ ሀሳቦችን አፈጻጸም መከታተል | * የተደረጉ ክትትሎች ብዛት<br>* ይፋ የተደረጉ የውሳኔ ሀሳብ ያካተቱ የክትትል ሪፖርቶች ብዛት | * 4 ክትትሎች<br>* 4 ክትትል ሪፖርቶች ከውሳኔ ሀሳብ ጋር | | | | | ዋና መ/ቤት፣ ሁሉም ቀ/ጽ/ቤቶች | |
| 3.4.2 | የህጻናት መብቶች በማሳደጊያዎች፣ በጤና ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶች፣ ማረሚያ ቤቶች ፣ መሳደጊያ እና ሌሎች ተቋማት መከበራቸውን በመከታተል ምክረ ሃሳቦችን መስጠትና አፈጻጸማቸውን መከታተል | *የተደረጉ ክትትሎች ብዛት<br>* ይፋ የተደረጉ የውሳኔ ሀሳብ ያካተቱ የክትትል ሪፖርቶች ብዛት | * 4 ክትትሎች<br>* 4 sክትትል ሪፖርቶች ከውሳኔ ሀሳብ ጋር | | | | | ዋና መ/ቤት፣ ሁሉም ቀ/ጽ/ቤቶች | |
| 3.4.3 | * የጉትጎታና የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት | *የምክክር ውይይቶች ብዛት | * 2 የምክክር መድኮች<br>*የሚድያ ሽፋን | | | | | ዋና መ/ቤት፣ ሁሉም ቀ/ጽ/ቤቶች | |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | *የክትትል ግኝቶችንና የውሳኔ ሀሳቦችን በስፋት ማሰራጨትና ማስተዋወቅ | * የሚድያ ሽፋን | መጨመር | | | | | | |
| 3.4.4 | የህጻናት መብቶችንና የጾታ እኩልነትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊነት የሚከታተሉ አካላት የሚያወጧቸውን ምክረ ሃሳቦችና አጠቃላይ ማብራሪያዎችን አፈጻጸም መከታተል | *የተደረጉ ክትትሎች ብዛት<br>*የክትትል ሪፖርቶች ብዛት | * 4 ክትትሎች<br>* 4 ክትትል ሪፖርቶች ከውሳኔ ሃሳብ ጋር | | | | | ዋና መ/ቤት | |
| 3.4.5 | አፈጻጸማቸውን ለመገምገም የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | *የምክክር መድረኮች ብዛት<br>* የሚዲያ ሽፋን ደረጃ<br>*የመንግስት አካላት የቁርጠኝነት ደረጃ | * 1 ወርክሾፕ<br>*የሚዲያ ሽፋን መጨመር | | | | | | |
| 3.4.6 | ሰነዶቹን ወደ ሀገራዊ ቋንቋ ማስተርጎም (የባለሙያ ክፍያ) | ወደ ሀገራዊ ቋንቋ የተተረጎሙ ሰነዶች ብዛት | 1 ሰነድ | | | | | ዋና መ/ቤት | |
| 3.4.7 | የተተረጎሙትን ሰነዶች ማሳተምና ማሰራጨት | የታተሙና የተሰራጩ ሰነዶች ብዛት | 200 ሰነዶች መታተምና መሰራጨት | | | | | ዋና መ/ቤት | |
| 3.4.8 | የኮሚሽኑን ባለሙዎች፣ ሲቪል ማኅበረሰብ አባላት እና ሕግ አውጪዎችን በሴቶችና ህጻናት መብቶች ሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና መስጠት | *የስልጠና ማኑዋል መዘጋጀት<br>*የተዘጋጁ ስልጠናዎች ብዛት<br>*የሰልጣኞች ብዛት<br>*የሰለጠኑ የሲቪል ማኅበረሰብ አባላት ብዛት | * 1 training manual developed<br>* 1 training organized<br>* 15 staff trained<br>* 15 CSO trained | | | | | ዋና መ/ቤት | |
| **3.5** | **አብይ ተግባር** 5፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተጠናከረ ግንኙነት መፍጠር | | | | | | | | |
| 3.5.1 | ሴቶች እና ህጻናት  መብቶች ላይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትንና | *ባለድርሻ አካላትን የሚዘረዝሩ ሪፖርቶች | * 9 ባለድርሻ አካላትን የሚዘረዝሩ ሪፖርቶች | | | | | ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች | |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | የሚያከናውኑትን ተግባራት የሚዘረዝሩ 9 (ማፒንግ) ሰነዶች ማዘጋጀት (የባለሙያ ክፍያ) | * የቁልፍ ባለድርሻ አካላት ቁጥርና የሚያከናውኑትን ተግባራት ዝርዝር መኖር | * 180 ቁልፍ ባለድርሻ አካላት መለየት | | | | | | |
| 3.5.2 | በተዘጋጀው ማፒንግ መሰረት ግንኙነቶችን መመስረት (ማጠናከር) እና የጋራ ስራዎችን ለመለየት የሚያስችል ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣ አፈጻጸሙን መከታተል (ከአጋርነት ስራ ክፍል ጋር በመሆን) | *የምክክር መድረኮች ብዛት<br>*በምክክር መድረኮች የተሳተፉ የቁልፍ ባለድርሻ አካላት | * 9 የምክክር መድረኮች<br>* 180 ቁልፍ ባለድርሻ አካላት | | | | | ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች | |
| 3.5.3 | አብሮ መስራትን የሚያጠናሩ የጋራ ፕሮጀክቶችን መንደፍና መተግበር መጀመር | የጋራ ፕሮጀክቶች ብዛት | 9 የጋራ ፕሮጀክቶች | | | | | ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች | |
| 3.5.4 | በሴቶች እና በህጻናት መብቶች ላይ የሚሰሩ አህጉራዊና ዓለም አቀፋ አካላትን እና መከናወን የሚችሉ ተግባራትን ከጊዜ ሰሌዳ ጋር በመለየት ግንኙነቶች መጀመር | * በሴቶች እና በህጻናት መብቶች ላይ የሚሰሩ አህጉራዊና አለምአቀፋዊ አካላትን የለየ ሪፖርት<br>*የተጀመሩ ግንኙነቶች ብዛትና አይነት | 1 ሪፖርት | | | | | ዋና መ/ቤት | |
| **3.6** | **አብይ ተግባር 6፡** በሴቶችና በህጻናት መብቶች ላይ የተሻለ ተቋማዊ አቅም መገንባት | | | | | | | | |
| 3.6.1 | የ ጸረ-ጾታዊ ትንኮሳ ፖሊሲ እንዲተገበር ስልጠና መስጠትን ጨምሮ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | *የኣሰልጣኞች ስልጠና ብዛት<br>* በ ጸረ-ጾታዊ ትንኮሳ ፖሊሲ ላይ የተሰጠ ስልጠናዎች ብዛት<br>*የሰለጠኑ ሰራተኞች ብዛት | * 1 የኣሰልጣኞች ስልጠና<br>* 9 ስልጠናዎች<br>* 30 የሰለጠኑ ሰራተኞች | | | | | | |
| 3.6.2 | ስርኣተ ጾታን በኣግባቡ መስረጽን የሚከታተል ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጣ ቡድን ማቋቋምና ማጠናከር | የቡድን መቋቋምና ስብጥር | *1 ቡድን *በቡድኑ እስፈላጊው የስራ ክፍሎች መካተት | | | | | ዋና መ/ቤትና የተመረጡ ቅ/ጽ/ቤቶች | |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| 3.6.3 | በአመት ሁለት ጊዜ የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ ማዘጋጀትና ውሳኔ ሃሳቦች መተግበራቸውን መከታተል (ከአጋርነት ስራ ክፍል ጋር በመሆን) | *የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ ብዛት<br>*የክትትል ስራዎች መካሄድ | *2 የአፈጻጸም ግምገማ መድረኮች<br>*በክትትል ስራዎች የተስተካከሉ አሰራሮች | | | | | ዋና መ/ቤትና | |
| 3.6.4 | ለኮሚሽኑ ሰራተኞች በሀጻናት መብት ክትትል እና ማካተት ላይ የ 5 ቀን የ አሰልጣኞች ስልጠና መስጠት ((ከፕሮግራም እና አጋርነት ጋር በመተባበር)) | * የተዘጋጁ ስልጠናዎች ብዛት<br>*የሰልጣኞች ብዛት | * 1 ስልጠና<br>*50 ሰልጣኞች | | | | | ዋና መ/ቤትና | |
| 3.6.5 | የስርአተ ጾታ ማስረጽ ስልጠና ለ30 የኮሚሽኑ ሰራተኞች መስጠት (ከሰው ሃብት ጋር በመተባበር) | *የስርኣተ ጾታ ማስረጽ ስልጠናዎች ብዛት<br>* የሰልጣኞች ብዛት | * 1 ስልጠና<br>* 30 ሰልጣኞች | | | | | ዋና መ/ቤትና | |
| 3.6.6 | የህጻናት መብቶች አፈጻጸም መከታተያ ማኑዋል ዝግጅት /ማሻሻል (ከሰብአዊ መብቶች ትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር) | *የስልጠና ማኑዋል | 1ማኑዋል | | | | | ዋና መ/ቤትና | |
| 3.6.7 | በ UNCRC, CEDAW, UPR የሚሰጡ ምክረሃሳቦን አፈጻጸም ለመከታተል በተዘጋጀው መመሪያና ቼክሊስት ላይ ለ 30 የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት (ከሰብአዊ መብቶች ትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር) | *የተዘጋጁ ስልጠናዎች ብዛት<br>*የሰልጣኞች ብዛት | * 1 ስልጠና<br>* 30 ሰልጣኞች | | | | | ዋና መ/ቤትና | |
| 3.6.8 | ለሆትላይን ካውንስለሮች የተግባቦትና ህጻናት ተኮር መረጃ አያያዝ ስልጠና መስጠት | *የተዘጋጁ ስልጠናዎች ብዛት | 1 ስልጠና | | | | | ዋና መ/ቤትና | |
| 3.6.9 | የሆትላይን አገልግሎት 18 ቴዝ ማናጀሮች 9 ወርሀዊ የግምገማ ስብሰባዎች | የግምገማ ስብሰባዎች ብዛት | 1 ግምገማ | | | | | ዋና መ/ቤትና | |
| | ጠቅላላ | የመንግስት ጠቅላላ በጀት ድምር- ብር፤ 635,597<br>የፕሮጀክት ጠቅላላ በጀት ድምር- ብር ፤ 14,879,476<br>የሁለቱም ድምር- ብር ፤ 15,515,073 | | | | | | | |

**ፕሮግራም መስክ 4፡ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች አፈፃፀም ይጠናከራል፤ የመብቶች ጥሰትም ውጤታማ መፍትሄ ያገኛል፤**

**የሥራ ክፍል፡** <u>የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች</u>

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| **4.1** | **አብይ ተግባር 1፡** የሕግ ማዕቀፍ እና አፈጻጸሙ ከአህጉራዊ እና አለም አቀፋዊ ስምምነቶች እና መስፈርቶች ጋር እንዲጣጣም ማድረግ | *በሕግ ማዕቀፍ እና አፈጻጸም ክፍተቶች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ብዛት<br>*የተሰጡና የተተገበሩ ምክረ ሃሳቦች ብዛት<br>*የተዘጋጁ የውትወታ የምክክር መድረኮች ብዛት<br>*የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት አይነትና ብዛት<br>*የሚድያ ሽፋን | | | | | | | የሕግ ማዕቀፍ እና አፈጻጸሙ ከአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች እና ስታንዳርዶች ጋር መጣጣም |
| 4.1.1 | ብሄራዊ ሕጎች አካል ጉዳተኞች በዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች እና መስፈርቶች ከተጎናፀፏቸው መብቶች ጋር ያላቸውን መጣጣም የሚያሳይ የግምገማ ጥናት ማካሄድ<br>*የምክረ ሃሳቦችን ተግባራዊነት መከታተል (የባለሙያ ክፍያ) | *ሕጉና አተገባበሩ ላይ ክፍተቶችን የሚያሳይ የጥናት ሪፖርት | *1 የጥናት ውጤት ማቅረብ | | | | | ዋና መ/ቤት | *1 የጥናት ውጤት ቀርቧል |
| 4.1.2 | የግምገማ፣ የውትወታ እና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት | *የግምገማ እና የውትወታ መድረኮች ብዛት<br>*የተሳታፊዎች ብዛት | *1 መድረክ ማዘገጀት<br>* 50 ሰዎችን ማሳተፍ | | | | | ዋና መ/ቤት | *1 መድረክ ተዘጋጅቷል<br>* 50 ሰዎች ተሳትፈዋል |
| 4.1.3 | የጥናቱን ውጤት ማስተዋወቅ እና በስፋት ማሰራጨት (ድረ-ገጽ መጠቀም፣ ሪፖርቶች እና መግለጫዎችን ማዘጋጀትና | *የሚድያ ሽፋን መጠን | *ከፍ ያለ የሚድያ ሽፋን ማግኘት | | | | | ዋና መ/ቤት | *ከፍ ያለ የሚድያ ሽፋን |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | እንዲዘገቡ ማድረግ) | | | | | | | | |
| 4.1.4 | የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እያከናወነ ባለው ሁሉን አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ሕግ (comprehensive disability law) የማርቀቅ ሂደት ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ | *የተሳትፎ መጠን | *ከፍ ያለ ተሳትፎ ማድረግ | | | | | ዋና መ/ቤት | *ከፍ ያለ ተሳትፎ ተደርጓል |
| 4.1.5 | በሃገር ውስጥ ተፈናቃዮች ላይ አተኩሮ በአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ላይ በግጭት ጊዜ ስለሚደርስ ስልታዊ የሙብት ጥሰት ምርመራ (investigation on systemic human rights violation) ማካሄድ<br>*የምክረ ሃሳቦችን ተግባራዊነት መከታተል | *በክልሎች የተከፋፈለ የክትትሎች ቁጥር<br>*ግልጽ የሆኑ ምክረ ሃሳቦች | *4 የክትትል ተልዕኮዎች በ 4 የተመረጡ ክልሎች ማካሄድ | | | | | ዋና መ/ቤት ከ ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | *4 የክትትል ተለዕኮዎች በ 4 የተመረጡ ክልሎች ተካሂደዋል |
| 4.1.6 | የምክክር መድረኮች ማዘጋጀት | *የመድረኮች ብዛት<br>*የተሳታፊዎች ብዛት | *5 መድረኮችን ማዘጋጀት<br>*250 ሰዎችን ማሳተፍ | | | | | ዋና መ/ቤት ከ ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | *5 መድረኮች ተዘጋጅቷል<br>*250 ሰዎች ተሳትፈዋል |
| 4.1.7 | የክትትሉን ግኝቶች እና ምክረ ሃሳቦች ማስተዋወቅ እና በስፋት ማሰራጨት (ድረ-ገጽ መጠቀም፣ ሪፖርቶች እና መግለጫዎችን ማዘጋጀትና እንዲዘገቡ ማድረግ) | *የተላለፉ መልእክቶች ብዛት<br>*የሚዲያ ሽፋን | *4 መልእክቶች ማስተላለፍ<br>*ከፍ ያለ የሚዲያ ሽፋን እንዲኖር ማድረግ | | | | | ዋና መ/ቤት ከ ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር | *4 መልእክቶች ተላልፈዋል<br>*የተሻለ የሚዲያ ሽፋን ታይቷል |
| **4.2** | **አብይ ተግባር 2፡** ባለግዴታዎች የአካል ጉዳተኞችን | *የክትትል እና የጉብኝት ሪፖርቶች ብዛት | | | | | | | ባለግዴታዎች የአካል ጉዳተኞችን እና |

| ተ.ቀ. | ዋና ዋና ሥራዎች በቁልፍና አበይት ተግባራት ስር | መለኪያ | ዒላማ | ክዋኔው የሚፈፀምበት ጊዜ | | | | ፈጻሚ አካል | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | |
| | እና የአረጋውያንን መብቶች እንዲያከብሩ እና እንዲያስጠብቁ የተሻለ ግንዛቤ ማስጨበጥ | *የክትትል ሪፖርቶች ብዛት<br>*የተሰጡና የተተገበሩ ምክረ ሃሳቦች ብዛት<br>*ከባለግዴታዎች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ብዛት | | | | | | | የአረጋውያንን መብቶች በማስከበር እና በማስጠበቅ ረገድ መሻሻልን አሳይተዋል |
